# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 84ኛ ዓመት ቁጥር 056 ጥቅምት 26 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## “የሃይማኖት ተቋማት አብሮ የመኖር እሴቶችንና ማኅበራዊ ትስስሮችን ማጠናከር ይገባቸዋል”

- አምባሳደር ታዬ አፅቀ ሥላሴ
የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት



**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡-የሃይማኖት ተቋማት አብሮ የመኖር እሴቶችንና ማኅበራዊ ትስስሮችን በማጠናከር ለሠላም ግንባታ የበኩላቸውን ሊወጡ ይገባል ሲሉ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት አምባሳደር ታዬ አፅቀ ሥላሴ ገለጹ።

የሠላም ሚኒስቴር በዩናይትድ ዓረብ ኢምሬትስ ከሚገኘው ከመሐመድ ቢን ዛይድ ፎር ሁማኒቲ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ያዘጋጀው ዓለም አቀፍ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ትላንት መካሄድ ጀምሯል።

የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ በጉባኤው መክፈቻ ላይ እንደገለጹት፤ የሃይማኖት ተቋማት የመቻቻል፣ አብሮ የመኖር እሴቶችና ማኅበራዊ ትስስሮች በማጠናከር በሠላም ግንባታው ላይ ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል።

በአሁኑ ወቅት ዓለም ላይ የጽንፈኝነትና የመከፋፈል ሀሳብ አብሮ ለመኖር አደጋ እየሆነ መቷል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፣ ሃይማኖት ተቋማት የጽንፈኝነትና የመከፋፈል ሀሳብን ለማስወገድ በቁርጠኝነት ሊሠሩ እንደሚገባ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ ለዘመናት በሃይማኖቶች መካከል መቻቻልንና አብሮ መኖርን ያሳየች ሀገር መሆኑዋን ጠቅሰው፣ ክርስትናን ቀድማ የተቀበለች እና በስደት የመጡ ሙስሊሞችን ያስተናገደች ሀገር መሆኑዋን ገልጸዋል።

ሀገሪቱ ብዙኃ ሃይማኖቶች ተከባብረው በጋራ የሚኖሩባት በመሆኑ ለዓለም ትልቅ ምሳሌ እንደሆነች በመግለጽ፣ የሃይማኖት ተቋማቱ በሀገረ መንግሥት ግንባታ ላይ ሚናቸው የላቀ መሆኑንም ተናግረዋል።

‹‹የሃይማኖቶች መቻቻልና በጋራ መኖር የምንናፍቃትን ዓለም

“የሃይማኖት ተቋማት አብሮ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ለሕገ መንግሥት ትርጉም የሚቀርቡ ጉዳዮች የትኞቹ ናቸው?

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

ሁሉም ሕጎች በራሳቸው ምሉዕ ባለመሆናቸው፣ ሕጎችን በተገቢው የአተረጓጎም ሥርዓት ተርጉሞ ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ መሆኑን የሕግ ምሁራን ያስረዳሉ። የየሀገሩ የበላይ የሆነው ሕገ መንግሥት ፍጹም ገለልተኛና የሕገ መንግሥትን የመተርጎም ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች ባሉት የሕገ መንግሥት ተርጓሚ አካል ሊተረጎም እንደሚገባውም ይታመንበታል። ለዚህም ሀገራት ሕገ መንግሥትን የሚተረጉሙ ተቋማት አሏቸው።

በኢትዮጵያም ሕገ መንግሥትን የመተርጎም ሥልጣን ለኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አጣሪ ጉባዔ ጽሕፈት ቤት የተሰጠ ሥልጣን ነው። ጽሕፈት ቤቱ የቀረበለት አቤቱታ የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያሻው መሆኑን ካረጋገጠና የሕገ መንግሥት መብት ጥሰት ተፈጽሞበታል ብሎ ካመነ የውሳኔ ሐሳቡን

ለሕገ መንግሥት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ሀገራት በራሳቸው ገንዘብ መገበያየትን ለምን መረጡ?

**ተስፋ ፈሩ**




ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሀገራት ዶላርን ገሸሽ በማድረግ በራሳቸው ገንዘብ የመገበያየት (Currency swap) ስምምነቶች መፈራረማቸውን የሚገልጹ ዜናዎች መስማት እየተለመደ መጥቷል። በተለይም የብሪክስ አባል አገራት ይህን ስምምነት ተፈራርመው በራሳቸው ገንዘብ ግዙፍ የንግድ ልውውጦችን እያካሄዱ ይገኛሉ።

ኢትዮጵያም ቁልፍ ከሆኑት የልማት አጋሮቿ የተባበሩት ዓረብ ኤሚሬቶች እና ቻይና ጋር ተመሳሳይ ስምምነት መፈራረሟ ይታወሳል። ለመሆኑ ሀገራት በራሳቸው ገንዘብ መገበያየትን እየመረጡ ያሉበት ምክንያት ምንድን ነው? ኢትዮጵያ እንዲህ ያለውን ስምምነት መፈረሟ የሚኖረው ፋይዳስ ምን ይመስላል ?

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ቆስጠንጢኖስ በርሔ (ዶ/ር) እንደሚናገሩት በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ማግስት የዓለም ኢኮኖሚን ለማረጋጋት በሚል እ.አ.አ በ1944 የዓለም ባንክ እና የዓለም የገንዘብ ድርጅት ሲቋቋሙ ሀገራት በምን ይገበያዩ የሚል ጥያቄ ተነሳ። በወቅቱ አንድ ሀገር ከሌላ አገር የሚገበያየው በወርቅ ነበር። የሁለቱን ድርጅቶች መመሥረት ተከትሎ በወርቅ ክፍያ ከመፈጸም ይልቅ ወርቅን መሠረት በማድረግ (Gold standard) በመመሥረት ከፍተኛ የወርቅ ክምችት ያለው ማዕከላዊ ባንክ ገንዘብ በዓለም አቀፍ ደረጃ መገበያያ ይሁን የሚል ውሳኔ ላይ ተደርሷል።

ሁለተኛው የዓለም ጦርነት እንግሊዝን ጨምሮ አብዛኞቹን የአውሮፓ ሀገራት ለከፍተኛ ወጪ ዳርጎ ስለነበር ጦርነቱ ብዙም ያልነካት አሜሪካ ከፍተኛ የወርቅ ክምችት ይዛ በመገኘቷ ዶላር በሀገራት መካከል የሚካሄድ ግብይት ማቀላጠፊያ እንዲሆን መወሰኑን የሚያወሱት ቆስጠንጢኖስ (ዶ/ር)፤ ከዚያ በኋላም አሜሪካን አምባገነን እንደሆነች ይጠቅሳሉ።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው እንደሚያብራሩት፤ ዶላር የዓለም መገበያያ መሆኑ የራሳቸው ገንዘብ ስለሆነ አሜሪካኖችን ነው የሚጠቅመው። የአሜሪካ መንግሥት ከባንኮች የተበደረው ዕዳ ወደ 33 ትሪሊየን ዶላር ደርሷል። የዋጋ ግሽበት እና የኢኮኖሚ ውድቀት ስለሚያመጣ በአንድ ጊዜ አያደርጉትም እንጂ የተጠቀሰውን የገንዘብ መጠን በኤሌክትሮኒክ አትመው ቢለቁ ከዕዳ ነፃ መሆን ይችላሉ። ሌሎች ሀገራት ግን ዕዳ ካለባቸው ዶላር ፈልገው ነው መክፈል ያለባቸው። ስለዚህ ከዚህ ጫና ለመላቀቅ ነው ሀገራት በራሳቸው ገንዘብ ለመገበያየት ስምምነቶችን እየተፈራረሙ ይገኛሉ።

በዓለም የንግድ ሥርዓት እስከ 80 በመቶ የገንዘብ ልውውጥ የሚደረገው በአሜሪካን ዶላር ነው። ሀገሮች ገንዘባቸውን ወደ ዶላር ለመቀየር ከፍተኛ ኮሚሽን ይከፍላሉ የሚሉት ቆስጠንጢኖስ (ዶ/ር)፤ አሜሪካ

ሀገራት በራሳቸው ገንዘብ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# የኢኮኖሚ ማሻሻያው አልሚዎች ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች መፍትሔ እየሰጠ መሆኑ ተገለጸ

**ሞገስ ፀጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በመንግሥት የተወሰዱ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች አልሚዎች ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች መፍትሔ እየሰጠ መሆኑን የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን አስታወቀ።

ኮርፖሬሽን የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽንና ማርኬቲንግ ዘርፍ ምክትል ሥራ አስፈጻሚ አቶ ዘመን ጁነዲን እንደገለጹት፤ ባለፉት አምስት ዓመታት መንግሥት በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ለሚያለሙ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች በርካታ ማበረታቻዎችን አድርጓል። በመንግሥት የተወሰዱ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች አልሚዎች ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች መፍትሔ እየሰጠ ነው።

ከውጭ ምንዛሪ እጥረት ጋር በተያያዘ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ገብተው ለማልማት ችግር ነበረባቸው ያሉት አቶ ዘመን፤ የምንዛሪ እጥረቱ በመቀረፉ ለአልሚዎች ምቹ ሁኔታ እንደፈጠረና የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችም በመላ ሀገሪቷ በሚገኙ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ በስፋት እየተሳተፉ መሆናቸውን ተናግረዋል።

በተለይ በጨርቃጨርቅ፣ በግብርና ማቀነባበር፣ በፋርማሲቲካል፣ በመኪና መገጣጠሚያና በሌሎች ዘርፎች የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች መሠማራታቸውን ገልጸዋል። እንዲሁም በተደረገላቸው ትንሽ ድጋፍ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ መሆን መቻላቸውንም አመልክተዋል።

እንደ አቶ ዘመን ገለፃ፤ መንግሥት የወሰዳቸው የኢኮኖሚ ማሻሻያዎችን ጨምሮ ከውጭ ምንዛሪ ጋር ያለውን ችግር መፍታት በመቻሉ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍላጎት ጨምሯል። ባለፉት ሁለት



አቶ ዘመን ጁነዲን

ሳምንታት ውስጥ በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ የቻይናና የአሜሪካ ባለሀብቶች የለማ መሬት ወስደዋል። በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ካሉ ሼዶች ውስጥ 86 በመቶ በአልሚዎች ተይዘዋል። የኢንቨስትመንት መዳረሻዎችን ከብሪክስ ሀገራት ጋር የማስፋት ሥራ እየተሠራ ሲሆን ከአባል ሀገራቱ በርካታ ባለሀብቶች ወደ ኢንቨስትመንት ለመግባት በሂደት ላይ ናቸው።

የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ኢንቨስትመንትን ከማነቃቃትና ከሚፈጥሩት የሥራ ዕድል በተጨማሪ ተኪ ምርቶች ላይ ትልቅ አስተዋፅዖ እያደረጉ መሆኑን በመጥቀስ፤ የተዛባውን የወጭና የገቢ ንግድ በማስተካከል ረገድ ሚናቸው ከፍተኛ መሆኑን አብራርተዋል።

በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ከውጭ ይገባ የነበረውን የፀጥታ አካላት አልባሳትን ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ መተካት መቻሉ በማሳያነት ጠቅሰዋል። በተጨማሪም ለቢራ አገልግሎት የሚውለውን የገብስ ብቅል በሀገር ውስጥ መተካት መቻሉ ባሌና አርሲ ለሚገኙ 60 ሺህ አርሶ አደሮች የገበያ ትስስር እንደፈጠረላቸው ተናግረዋል።

የጅማ ኢንዱስትሪ ፓርክ በአካባቢው ያለውን አቮካዶ በማቀነባበር 30 ሺህ ለሚደርሱ አምራቾች የገበያ ትስስር ፈጥሯል ያሉት ምክትል ሥራ አስፈጻሚው፤ ከአቦካዶ ዘይትና ቅባት በማምረት ለአውሮፓና ለአሜሪካ ገበያ እያቀረቡ መሆናቸውን ጠቁመዋል። በዚህም ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እየተገኘ መሆኑን አመልክተዋል።

በባሕርዳር ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ከአኩሪ አተር የምግብ ዘይት በማምረት ሙሉ ለሙሉ ለውጭ ገበያ የማቅረብ ሥራ መጀመሩን ጠቅሰው፤ በዚህም ዘጠኝ ሺህ ስምንት መቶ ለሚደርሱ አርሶ አደሮች ዘላቂ የገበያ ትስስር መፍጠር መቻሉን አስረድተዋል።

በፓርኮች የተሰማሩ አልሚዎች የኢንቨስትመንት ምሕዳሩን ከማነቃቃት በተጨማሪ የተኪ ምርት ላይ አስተዋፅዖ እያደረጉ ነው ያሉት አቶ ዘመን፤ ይህም እንደ ሀገር ለታሰበው የመዋቅራዊ ሽግግር ዋነኛ ተዋናይ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ኢንዱስትሪያሊስቶች እንዲፈጠሩ ማድረጉን ጠቁመዋል። ፓርኮች በቂ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የውሃ አቅርቦት የተሟላላቸውና ደኅንነታቸው የተጠበቀ በመሆኑ ከሌሎች የኢንቨስትመንት ማዕከላት ተመራጭ ስለመሆናቸው ገልጸዋል።

# የሃይማኖት ተቋማት የመቻቻል ትርክትን መገንባት ላይ መሥራት እንዳለባቸው ተገለጸ

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የሃይማኖት መሪዎችና ተቋማት የመቻቻል ትርክትን መገንባትና የተዛባ አመለካከትን ማረም ላይ ሊሠሩ እንደሚገባ ተገለጸ።

የሠላም ሚኒስትር አቶ ብናልፍ አንዱዓለም በመድረኩ ላይ እንደገለጹት፣ የሃይማኖት ተቋማት የመቻቻልን ትርክት ሊያበረታቱና ዜጎች በመተሳሰብ እንዲኖሩ ቁልፍ ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል።

ሃይማኖት የግለሰቦችንና የማኅበረሰቦችን እሴትና ባሕሪን የመቅረጽ አቅም ያለውና በተከታዮች ዘንድም ትልቅ ዋጋ ያለው ነው ያሉት ሚኒስትሩ፣ ሆኖም ግን በሃይማኖት ልዩነቶች ምክንያት በማኅበረሰቡ ዘንድ ብዙ መከፋፈሎችና ግጭት ሲነሳ ይስተዋላል ብለዋል።

ሃይማኖት የአንድነትና የጥንካሬ ምንጭ ሊሆን እንደሚችል ሁሉ ጥላቻንና ግጭትን ሊያበረታታ እንደሚችል ጠቅሰው፣ የተለያዩ አጥፊ ኃይሎች የተሳሳተ መረጃ በማሰራጨት የማኅበረሰቡን ሠላም ሲያደፈርሱ እንደሚስተዋልም ገልጸዋል።

ሁሉም የሃይማኖት ተቋማት የመቻቻልን ትርክት ሊያበረታቱና ዜጎች በመተሳሰብ እንዲኖሩ ማድረግ ተገቢ መሆኑን በመግለጽ፤ ተቋማቱ መንፈሳዊ ድጋፍን በማድረግ በማኅበረሰቡ ዘንድ አንድነትን በማበረታታት ቁልፍ



አቶ ብናልፍ አንዱዓለም

ሚናቸውን ሊወጡ እንደሚገባ አመላክተዋል።

የኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ጠቅላይ ፀሐፊ ቀሲስ ታጋይ ታደለ በበኩላቸው፣ ተቋማት ከምን ጊዜውም በላይ ተቀራርበው ለሰው ልጆች አንድነት፣ መከባበርና ሠላም በጋራ ሊሠሩ እንደሚገባ ጠቅሰዋል።

ልዩነቶች እንደተጠበቁና እንደተከበሩ ሆነው ዜጎች በመቻቻልና በመከባበር በሠላም ይኖሩ ዘንድ የሃይማኖት አባቶች ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል ያሉት ፀሐፊው፤ በዓለም ላይ የሚስተዋሉ አሳዛኝ ክስተቶችንና ሰቆቃዎች ለማስቆም



ቀሲስ ታጋይ ታደለ

የእረኝነት ኃላፊነት አለባቸው ብለዋል።

ችግሮችን ለማስወገድ አብሮ መኖርን፣ መቻቻልን፣ ፍትሕን ማስፈንን ጨምሮ፣ እኩልነትና ነፃነት ላይ በማተኮር መሥራት አስፈላጊ መሆኑን እና የሐሰተኛ መረጃ ሥርጭት፣ የተሳሳተ ትርክት፣ የኢ-ፍትሐዊነትና የእኩልነት እጦት ውጤት መሆናቸውን ገልጸዋል።

ከሃይማኖት አስተምሮም ሆነ ከሰብዓዊ ድንጋጌዎች አንጻር ሁሉም ሰው እኩልና የተከበረ ፍጡር ነው ያሉት ቀሲስ ታጋይ፤ ለደሀውና ለተቸገረው በእውነት መፍረድ፣ ለተገፋው ማዘን የሃይማኖት መመሪያና ግዴታ ነው ብለዋል።

ሁሉም ሃይማኖቶች ሠላምን፣ አንድነትን፣ ፍቅርን መረዳዳትን እንዲያስተምሩና እንዲሰብኩ ከፈጣሪ የተሰጣቸው ኃላፊነት መሆኑን ጠቅሰው፣ መለያየት ኃጢያት መሆኑን የሃይማኖት አባቶች በቃልና በተግባር በተከታዮቻቸው ማስገንዘብ እንዳለባቸውም ተናግረዋል።

የመሐመድ ቢን ዛይድ ዩኒቨርሲቲ ቻንስለር ከሊፋ ሙባረክ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፣ የጥላቻ ትርክትን በማስወገድ የአንድነት እሴቶችን ማሳደግ ያስፈልጋል።

በሃይማኖት ተቋማት መካከል የመነጋገር ባሕልን ማሳደግ አስፈላጊ ነው ያሉት ከሊፋ (ዶ/ር)፣ ተቋማቱ ልዩነቶችንና ግጭቶችን ለማስወገድ ትልቅ ሚና ይኖራቸዋል ብለዋል።

በሃይማኖቶች መካከል መቻቻልና አብሮ መፍጠር ለሠላም እወጃ በር የሚከፍት መሆኑን ጠቅሰው፤ በሕዝቦች መካከል ልባዊ የሆነ አንድነትን ለመፍጠር ተቋማቱ በትኩረት ሊሠሩ እንደሚገባቸውም ጠቁመዋል።

የሠላም ሚኒስቴርና የመሐመድ ቢን ዛይድ ዩኒቨርሲቲ በጋራ ለመሥራት የሚያስችላቸውን ስምምነት ተፈራርመዋል።

# ከመኸር እርሻ 615 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለመሰብሰብ እየተሠራ ነው

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- ከ2016/17 ዓ.ም የመኸር እርሻ 615 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለመሰብሰብ እየተሠራ መሆኑን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

የግብርና ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈፃሚ አቶ ከበደ ላቀው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2016/17 ዓ.ም የመኸር እርሻ በሁሉም ክልሎች 20 ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ሙሉ ለሙሉ በዘር በመሸፈን 615 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት የታቀደውን እቅድ ተግባራዊ በማድረግ የደረሱ ሰብሎችን በሰው ኃይልና በኮምባይነር የመሰብሰብ ሥራ እየተሠራ ነው።

በ2016/17 ዓ.ም የመኸር እርሻ በዘር ለመሸፈን የታቀደውን 20 ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ሙሉ ለሙሉ በዘር የመሸፈን ሥራን በማሳካት 615 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት በቆላና በደጋ የደረሱ ሰብሎችን የመሰብሰብ፤ ያልደረሱ ሰብሎች አስፈላጊውን እንክብካቤ የማድረግ፤ ሲደርሱ በጊዜያቸው እንዲሰበሰቡ ተገቢውን ዝግጅት የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል።

በሀገሪቱ የተለያዩ ቆላማ አካባቢዎች የደረሱ ሰብሎችን በሰው ኃይልና በኮምባይነር የመሰብሰብ ሥራ እየተሠራ እየተከናወነ መሆኑን ተናግረዋል። በ2016/17 ዓ.ም የመኸር እርሻ ከ20 ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬትን በበቆሎ፤ በማሽላ፣ በስንዴ፤ በጤፍ፣ በገብስና በመሳሰሉ ሰብሎች የመሸፈን ሥራ ተሠርቷል፤ ከተዘሩት የተለያዩ ሰብሎች ውስጥ የደረሱ ሰብሎችን በጊዜያቸውና በወቅታቸው የመሰብሰብ ሥራ በስፋት እየተሠራበት መሆኑን ተናግረዋል።

የምርት ብክነት እንዳይደርስ የደረሱ ሰብሎችን በጊዜያቸው፤ በወቅታቸው፣ በጥንቃቄ በሰው ኃይልና በቴክኖሎጂ ማለትም በግብርና መካናይዜሽን በመሰብሰብ ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል።

የደረሱ ሰብሎችን ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ እንዳያበላሻቸው ከኢትዮጵያ ብሔራዊ የሚትዎሮሎጂ ተቋም ጋር በቅንጅት በመሥራት ለአርሶ አደሩ መረጃ በፍጥነት እንዲደርሰው የማድረግ ሥራ እየተሠራ መሆኑንና አርሶ አደሩም ምርትና ምርታማነቱን ለማሳደግ ሰብሎችን በጊዜያቸው የመሰብሰብ ሥራ እየሠራ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ግብርናውን የማዘመን፣ ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ሥራ እየተሠራ ነው፤ እየተሠራ ያለውም ሥራ ትልቅ ውጤት እያስገኘ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

አርሶ አደሩ የደረሱ ሰብሎችን በመሰብሰብ በኩል እያነሳ ያለውን ንቁ ተሳትፎ አጠናክሮ መቀጠል አለበት ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

# ኢንተርፕራይዞቹ ለሀገር ኢኮኖሚ ልማት አስተዋፅዖዋቸውን ሊያሳድጉ ይገባል

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች በአዕምሯዊ ንብረት ዘርፍ ያላቸውን ግንዛቤ አሳድገው ለሀገር ኢኮኖሚ ልማት የሚያበረክቱትን አስተዋፅዖ ከፍ ሊያደርጉ እንደሚገባ የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን አስታወቀ።

የአዕምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን ከዓለም አቀፉ የአዕምሯዊ ንብረት ድርጅት ጋር በመተባበር ያዘጋጀው ሀገር አቀፍ የአዕምሯዊ ንብረት ሳምንት ትናንት ተከፍቷል።

በመርሐ ግብሩ መክፈቻ የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አቶ ወልዱ ይመስል እንዳሉት፤ በኢኮኖሚ ያደጉ ሀገራት አሁን ለደረሱበት ደረጃ በአዕምሯዊ ዘርፍ ልማት ጠንክረው በመሥራታቸው ምክንያት ነው። በትግበራው ጃፓን፣ ታይዋን፣ ደቡብ ኮሪያ በዘርፉ በቀዳሚነት የሚገለጹ ሀገራት መሆናቸውንም በአብነት ይጠቀሳሉ።

ሀገራቱ የመጀመሪያው የእድገት ጉዟቸው ከሀገራዊ ምርታቸው እስከ 90 በመቶ በእነዚህ ተቋማት ተመርቶ ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያ የሚቀርብበት ሁኔታ እንደነበር አስታውሰዋል። ኢንተርፕራይዞቹ ለወጣቱ ሰፊ የሥራ ዕድል በመፍጠር ከፍተኛ አስተዋፅዖ ማበርከታቸውንም ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ በሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ሁለተኛው ምዕራፍ ላይ እንደምትገኝ በመጥቀስ፤ ዘርፉ የሀገር ኢኮኖሚን የሚለውጥበት ምቹ ሁኔታ እንዳለው አመልክተዋል።

ነገር ግን ኢንተርፕራይዞቹ ተሳትፏቸው ዝቅተኛ በመሆኑ ተቋማቱ በአዕምሯዊ ንብረት በተንቀሳቃሽ ሃብት ረገድ በትኩረት መሥራት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።

በአዕምሯዊ ንብረት ዓለም በዘርፉ የደረሰበትን ደረጃ በመገንዘብ ኢንተርፕራይዞቹ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባቸው ተናግረዋል።

በአዕምሯዊ ንብረት ሥርዓት መመዝገባቸው የገበያ ተወዳዳሪነትን በከፍተኛ ሁኔታ ያሳድግላቸዋል፣ የምርት ዋጋን ይጨምራል፣ የገንዘብ ችግራቸውንም እንደሚፈታ ተናግረዋል። የፈጠራ ባለሙያዎች የፈጠራ ሥራዎቻቸውን አስይዘው የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኙበት ሥርዓት እየተገነባ እንደሚገኝ በመጠቆምም፤ ብዙ ባንኮች እንዲጠቀሙበት እንፈልጋለን ብለዋል።

በኢንተርፕራይዞቹ ጥራት ያላቸው ምርቶች እንዲመረቱ እና ምርቶቹ ዓለም አቀፍ ተፈላጊ እንዲሆኑ ማገዝ እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ምክትል ዳይሬክተር አቶ ጳውሎስ በርጋ ኢንተርፕራይዞቹ ሰፊ የሥራ ዕድል ፈጠራና ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በመተካት ጉልህ አስተዋፅዖ እያበረከቱ እንደሚገኙ ተናግረዋል። አጠቃላይ 74 ቢሊዮን ብር ካፒታል ማስመዝገባቸውን፣ ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሥራ ዕድል መፍጠራቸውን፣ በሃገር ምርት መኩራት እንዲቻል  እንዲሁም በእውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር አስተዋፅዖ ማድረጋቸውን አመልክተዋል።

የዓለም አቀፉ የአዕምሯዊ ንብረት የአፍሪካ ተወካይ ዳይሬክተር ሚስ ሎሬታ በበኩላቸው፤ መካከለኛ እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በሀገራዊ ምርት እና ሁለንተናዊ ልማት ወስጥ ከፍተኛ ሚና እንደሚያበረክቱም ተናግረዋል።

እንደርሳቸው ገለጻ፤ አዕምሯዊ ንብረት ለኢንተርፕራይዞቹ ሥራቸውን ለማቀላጠፍ እና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማስቻል ከፍተኛ አስተዋፅዖ አለው። የራሳቸው ብራንድ እንዲኖራቸው እና ዓለም አቀፍ የገበያ ተደራሽነት እንዲኖራቸው ለማስቻልም ጉልህ አስተዋፅዖ ያበረክታል።

## ባለሥልጣኑ ዘጠኝ...

**ከ2ኛ ገጽ የዞረ**

እንዲያገለግል መሰጠቱንም ተናግረዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ የአራቱም ክልሎች ማለትም ኦሮሚያ፣ ደቡብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሲዳማ አርሶ አደሮች ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስፈልጋቸውን በቴክኖሎጂ የታገዙ ግብዓቶች እንዲገዙ ተደርገዋል። ያረጁ የቡና ተክሎች አንስቶ በአዲስ በመተካት ምርት እና ምርታማነት ለማሳደግ እንቅስቃሴ ተደርጓል።

ከዚህ ቀደም አርሶአደሩ ያረጁ ቡናዎችን ለማንሳት የሚጠቀምበት መሣሪያ ኋላቀር በመሆናቸው ከአንዱ ቡና ወደ ሌላኛው ቡና በሽታዎች በቀላሉ ይተላለፉ እንደነበር ጠቁመዋል። ቡናውንም ለመቁረጥ ብዙ ጉልበት ይፈጅ እንደነበር በመጥቀስ፤ ይህን ለማስቀረት አዳዲስ የመጎንደያ (የመቁረጫ) ማሽን ለአርሶ አደሮች መሰጠቱን ጠቁመዋል።

አጠቃላይ አንድ መቶ ሠላሳ አንድ ሚሊዮን ብር በማውጣት ለአራቱም ክልሎች ግብዓቶች የተገዛ ሲሆን፤ ሁለት መቶ ሃያ አምስት ሞተራይዝድ መጋዝ፣ ሁለት መቶ ሃያ ዘመናዊ የጉድጓድ መቆፈሪያ፣ አስር ሺ የተጎነደለ ቡና ለመቀጠል የሚረዳ ማሽን  እና ሌሎች ግብዓቶች መቅረባቸውን ገልፀዋል።

# “የሃይማኖት ተቋማት አብሮ የመኖር እሴቶችንና...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

እውን ለማድረግ የሚያስችል ነው›› ያሉት አምባሳደር ታዬ፤ በዓለም ላይ ጽንፈኝነት እየጎላ በመምጣቱ ከሃይማኖት ተቋማት መፍትሔ የሚፈለግበት ጊዜ መሆኑን ገልፀዋል።

ሃይማኖት በዜጎች መካከል መከፋፈልን ለማስወገድ ድልድል ሆኖ እንደሚያገለግል ጠቅሰው፣ ጠንካራ የሆነ አንድነትን ለማምጣት ከሃይማኖት ተቋማት ትልቅ ሚና እንደሚጠበቅ ገልጸዋል።

የሃይማኖት ተቋማት የመቻቻል፣ አብሮ የመኖርና የመተሳሰብ እሴት በማጠናከር ረገድ ሚናቸው የጎላ በመሆኑ በጉባኤው የሃይማኖት ተቋማት ሀገራዊ አንድነትን በሚያጠናክሩበት፣ የጋራ ተግዳሮቶችን በጋራ ለመፍታት በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ በትኩረት መምከር እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

# ለሕገ መንግሥት ትርጉም የሚቀርቡ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ያቀርባል። የፌዴሬሽን ምክር ቤትም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 62 መሠረት ሕገ መንግሥቱን የመተርጎም ሥልጣን ተሰጠው በመሆኑ ጽሕፈት ቤቱ ያቀረበለትን የውሳኔ ሐሳብ አጣርቶ ውሳኔ ይሰጣል።

ይህ ቢሆንም ግን፣ ከሕገ መንግሥት ትርጉም ጋር የማይገናኙ አቤቱታዎች የአጣሪ ጉባዔውን ጊዜ እና የሰው ኃይል ብሎም በጽሕፈት ቤቱ ሊታዩ የሚገባቸውን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጉዳዮች ጊዜ እየተሻሙ እንዳሉ የጉባዔ ጽሕፈት ቤቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ ደሳለኝ ወዬሳ ይናገራሉ።

ዳይሬክተሩ እንዳስረዱት፣ የሕገ መንግሥት ትርጉም ምንነትና የሕገ መንግሥት መብት ጥሰት ሲባል ምን ማለት ነው የሚለው ላይ ከፍተኛ የግንዛቤ ክፍተት በመኖሩ ሳቢያ ተቋሙን ከፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ቀጥሎ ያለ የይግባኝ ፍርድ ቤት አድርጎ የመቁጠር አስተሳሰብ ይስተዋላል። በዚህ ሳቢያ ጉባዔ ጽሕፈት ቤቱ ከሕገ መንግሥት ትርጉም ጋር ተያያዥነት የሌላቸው በርካታ መዝገቦች እየቀረቡለት ይገኛሉ።

ጽሕፈት ቤቱ ኃላፊነቱ ሕገ መንግሥትን የመተርጎም እንጂ ሕግን የመተርጎም አይደለም ያሉት አቶ ደሳለኝ፣ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 78 መሠረት ሕግን የመተርጎም ሥልጣን ለፍርድ ቤቶች የተሰጠ ነው። ጉባዔው ደግሞ ከተሰጠው ሥልጣን ውጪ የመደበኛ ፍርድ ቤት ሥራን አይሠራም።

በጽሕፈት ቤቱ የጥናትና ምርምር ዳይሬክተር አቶ ከላሊ ኪሮስ፤ ወደ ጽሕፈት ቤቱ ከሚመጡ መዝገቦች መካከል ከ97 ከመቶ በላይ የሚሆኑት የሕገ መንግሥት ትርጉም አያስፈልጋቸውም ተብለው የሚመለሱ መሆናቸውን ያነሳሉ።

አቶ ከላሊ እንደሚሉት፤ ሁለት ተከራካሪዎች በፍርድ ቤት ተገቢውን ሂደት አልፈው ማስረጃ አቅርበው ፍርድ ቤቱ አሳማኝ የሆነውን ማስረጃና እና ክርክር ላቀረበው ወገን ከወሰነ በኋላ አንደኛው ወገን ለምን ለእኔ አልተወሰነልኝም በሚል መነሻ ሕገ መንግሥታዊ መብቴ ተጥሷል ብሎ አቤቱታውን ለጽሕፈት ቤቱ ያቀርባል። ይህ ሰው የተከራከረበት ጉዳይ ለምሳሌ የንብረት ጉዳይ ቢሆንና ንብረት የማፍራት መብቴ ተጥሷል ብሎ ቢመጣ ሕገ መንግሥቱ ንብረት የማፍራት መብትን የሰጠው ለሁለቱም ግራና ቀኝ አካላት እንጂ ለአንዱ ብቻ ሊሆን አይችልም፤ ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን የይዞታ ማረጋገጫ አሳማኝነት አረጋግጦ ፍርድ ከሰጠ ተገቢ ማስረጃ ላቀረበው አካል ተፈርዶለታል ማለት ነው። የተረታው ተከራካሪ ማስረጃው ትክክል አይደለም ወይም የተጭበረበረ ነው፤ ተገቢ ውሳኔ አይደለም ካለም አሳማኝ መከራከሪያ በመያዝ በይግባኝ ማቅረብና መከራከር ይችላል። እንዲህ ያለው ጉዳይ ሕገ መንግሥታዊ መብቴን ጥሷል በሚል ሊቀርብ የሚችለው አንድ ባለጉዳይ ክስህን ለፍርድ ቤት ማቅረብ አትችልም፣ እንዲህ ያለ ማስረጃ ማቅረብ አትችልም፣ ፍርድ ቤት ቆመህ መከራከር አትችልም ቢባል ነበር፤ ነገር ግን እሱን የሚያስደስት ውሳኔ ስላልተወሰነለት ብቻ ሕገ መንግሥታዊ መብቴ ተጥሷል የሚል አቤቱታ ሕግ መንግሥታዊ ሊሆን አይችልም።

የጽሕፈት ቤቱ ዋና ዳይሬክተር፤ የሕገ መንግሥት መብት ጥሰት ከተፈጸመባቸውና የሆኑ የሕገ መንግሥት ትርጉም የውሳኔ ሐሳቡን ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ያቀረበባቸውን ጉዳዮች መካከል ሁለቱን ለማሳያነት ይጠቅሳሉ። አንደኛው ለዜጎች የተሰጠውን የዋስትና መብትን የሚቃረን፣ ዜጎች ዋስትና መብታቸው በፍርድ ቤት እንዳይረጋገጥ የሚከለክለው የአደገኛ ቦዘኔ አዋጅ ሲሆን፣ ይህም ዜጎች በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጠላቸውን ፍትሕ የማግኘትና ዜጎችን መብት እና ነፃነት የሚጋፋ በመሆኑ፣ ዋስትና መብት መከልከሉ ሕገ መንግሥታዊ አይደለም በሚል የሕገ መንግሥት ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፤፡

ሁለተኛው የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዕጣ አወጣጥ ጋር የተያያዘ ሲሆን የዕጣ አወጣጥ መርሐ ግብሩ ክፍያቸውን ሙሉ በሙሉ ያጠናቀቁትን የሚመለከት ነው የሚል ጉዳይ ሲባል ይህ በዜጎች መካከል በሀብት፣ በዘር፣ በሃይማኖት ልዩነት መፍጠር በሕገ መንግሥቱ በግልጽ የተከለከለ በመሆኑና ከዚህም በተጨማሪ ከጋራ መኖሪያ ቤቶች ልማት ዓላማ ያፈነገጠ አሠራር መሆኑን አረጋግጦ የወጣውን የዕጣ አወጣጥ መመሪያ ኢ-ሕገ መንግሥታዊ ነው በማለት የውሳኔ ሐሳቡን ለፌደሬሽን ምክር ቤት አቅርቧል።

ጉባዔው ሥራ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ከቀረቡለትና ከተመለከታቸው ስድስት ሺ 283 መዝገቦች መካከል ትክክለኛ የሕገ መንግሥት መብት ጥሰት የተፈጸመባቸው መዝገቦች 138ቱ መሆናቸውን ያነሱት ዳይሬክተሩ፤ ጉባዔው ጋር መቅረብ የሌለባቸው ጉዳዮች ቁጥር ከፍተኛ መሆኑን ያመላክታሉ።

የጽሕፈት ቤቱ ተግባር ምንድነው የሚለው ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖር ለማስቻል በዚህ ዓመት ለጉባዔው የሚቀርቡ አቤቱታዎች ምን ምን መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው? የሕገ መንግሥት ትርጉም ጉዳይ የሆኑት የትኞቹ ናቸው? በሚሉት ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ እንደሚሰጥ የተናገሩት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ለዳኞች፣ ጠበቆች፣ የፍትሕ አካላትና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ለመስጠት የታቀደው የግንዛቤ ማስጨበጫ አቤቱታ አቅራቢዎች የሕገ መንግሥት መብት ጥሰትን ብቻ ላይተው ለጉባዔ ጽሕፈት ቤቱ እንዲያቀርቡ ያግዛል ተብሎ እንደሚጠበቅም ይናገራሉ።

አቶ ከላሊ በበኩላቸው፣ በጉባዔው የውሳኔ ሀሳብ አቅራቢነት የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሚያስተላልፋቸው ውሳኔዎች ለጽ/ቤቱ መቅረብ ያለባቸው ጉዳዮች የትኞቹ ናቸው ለሚለው ጥሩ አስረጂ መሆናቸውን ገልጸው፣ ነገር ግን ውሳኔዎችን የማሳተምና በበቂ መጠን ተደራሽ አለመሆናቸው አንዱ ክፍተት መሆኑን አንስተዋል። የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሚያስተላልፋቸው ውሳኔዎች በመጽሔት መልክ በበቂ መጠን ተደራሽ ቢደረግ በሕግ መተርጎምና በሕገ መንግሥት ትርጉም መካከል ያለውን ልዩነት ለመረዳትና ወደ ጽሕፈት ቤቱ መምጣት ያለባቸው አቤቱታዎች ምን አይነት መስፈርትን ሊያሟሉ ይገባል በሚለው ላይ ያለውን የግንዛቤ ክፍተት ለመሙላት እንደሚረዳ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

# ሀገራት በራሳቸው ገንዘብ መገበያየትን...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

በተለያዩ ሀገራት ላይ ማዕቀብ በመጣል ገንዘብ እንዳያንቀሳቅሱ ታደርጋለች። ሀገራት ይሄን ማዕቀብ ለመሸሽ ሲሉም በራሳቸው ገንዘብ መገበያየት ይፈልጋሉ። የዩክሬን ጦርነትን ተከትሎ ሩሲያን ከአውሮፓውያኑ የገንዘብ ማስተላለፊያ ስዊፍት ካወጧት በኋላ በራሳችን ገንዘብ እንገበያይ የሚለው ሀሳብ እየጎለበተ መምጣቱን ያስረዳሉ።

አያይዘውም፤ እንደ አሜሪካን ያሉ ሀገራት ከተፎካካሪዎቻቸው ጋር መፋጠጥ ውስጥ ሲገቡ ከጦርነት ባሻገር የሚያደርጉት ነገር ማዕቀብ መጣል ነው። አሜሪካ በኢራን እና ሩሲያ ላይ የምትጥለው ማዕቀብ እየጎዳ ያለው ሁለቱን ሀገሮች ብቻ ሳይሆን ከእነሱ ጋር የንግድ ልውውጥ የሚያደርጉ ሀገራትን ጭምር ነው። ይሄ ማለት በአንድ ሀገር ላይ የሚጣል ማዕቀብ በርካታ ሀገራትን ሥራ እንዳይሠሩ የማድረግ አቅም አለው ማለት ነው። የሚጥሉትን ማዕቀብ የሚያስፈጽሙበት ትልቁ ችሎታቸው የአሜሪካን ዶላርን እንዳይጠቀሙ መከልከል ነው። በራስ ገንዘብ መገበያየት ይህንን ማዕቀብ ጉልበት አልባ ያደርገዋል ብለዋል።

በተለይም የብሪክስ አባል ሀገራት በራሳቸው ገንዘብ ለመገበያየት ስምምነት እያደረጉ ያሉት የአሜሪካንን አምባገነንነት ለመገዳደር ነው። ሩሲያ ለቻይና የምትሸጠውን ነዳጅ ክፍያ በዩሃን ነው የምትቀበለው፣ ይህን ገንዘብ ከቻይና ለምታስገባቸው የተለያዩ ሸቀጦች ግዢ ትጠቀመዋለች። ይህ የአሜሪካንን ዶላር ከጫወታ ውጭ የሚያደርግ አካሄድ ነው። የብሪክስ ሀገራት ዋነኛ ግብ ሁሉም ሀገራት በሉዓላዊነት ተሳትፎ ኖሯቸው ዓለም በእኩልነት የምትተዳደርበትን ሁኔታ መፍጠር ነው ሲሉም ያክላሉ።

ኢትዮጵያ በራስ ገንዘብ ለመገበያየት ከሀገራት ጋር የምታደርገው ስምምነት የሚኖረውን ፋይዳ ሲያስረዱም፤ አሁን ባለው ሁኔታ ኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሪ ክፍተት አለ። ከሀገራት ጋር በራስ ገንዘብ መገበያየት የሚያስችል ስምምነት መፈረሙ ክፍተቱን ለመሸፈን ይረዳል ብለዋል።

የመንግሥት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች በተለያየ ጊዜ የሰጧቸው መግለጫዎች እና አስተያየቶች እንደሚያመለክቱት ኢትዮጵያ ከተለያዩ ሀገራት ጋር በራስ ገንዘብ ለመገበያየት ስምምነቶች መፈራረሟ በርካታ ጠቀሜታዎች የሚያስገኝ ነው።

ኢትዮጵያ እና ቻይና ብር እና ዩሃን በመጠቀም ያለ ዶላር በመካከላቸው ግብይት እና ኢንቨስትመንት ለማካሄድ ስምምነት በመፈረሙበት ወቅት የገንዘብ ሚኒስትሩ አሕመድ ሺዴ ባደረጉት ንግግር የስምምነቱ ግቡ የንግድ ልውውጥን ማሳደግ፣ የውጭ ኢንቨስትመንትን መሳብ፣ የውጭ ምንዛሪ እጥረትን መቅረፍ እና በኢትዮጵያ እና በቻይና መካከል ያለውን ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ማጠናከር ነው ብለዋል።

በተመሳሳይ መንገድ ኢትዮጵያ እና የተባበሩት ዓረብ ኤሜሬቶች ለግብይት የራሳቸውን ገንዘብ ለመጠቀም ሲስማሙ፣  ስምምነቱን የፈረሙት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ ማሞ ምሕረቱ በሰጡት አስተያየት፤ ሁለቱ ሀገራት በራሳቸው መገበያያ ገንዘብ ለመገበያየት መስማማታቸው ለኢትዮጵያ ተጨማሪ ፈንድ እንድታገኝ ያስችላታል። የምንጠቀመውን የወጪ ንግድ መገበያያ ገንዘብ አማራጭ ያሰፋልናል፤ እንዲሁም በመጪዎቹ ዓመታት በሁለቱ ሀገራት መካከል ያድጋል ተብሎ የሚጠበቀውን የንግድ እና የኢንቨስትመንት ግብይቶች ለማሳለጥ ይረዳናል ብለዋል።

የፖለቲካል ኢኮኖሚ ተንታኙ ሸዋፈራው ሽታውን በበኩላቸው፤ እ.አ.አ በ1991 ሶቭየት ኅብረት የምትባለዋ ግዙፍ ሀገር በይፋ ፍርክስክሷ ከወጣ በኋላ የዓለም ፖሊስ ሆና የተሰየመችው አሜሪካ ናት። ዓለም በአንድ ጡንቸኛ ሀገር የመመራቷ ነገር እያበቃ ይመስላል። አሁን ብሪክስ የሚባል ስብስብ ወደፊት እየመጣ ነው። የአሜሪካ ወዳጅ የሚባሉ ሀገራትም ቡድኑን እየተቀላቀሉ ይገኛሉ። ይህ ስብስብ የአሜሪካን ዶላርን ገሸሽ በማድረግ አባላቱ በራሳቸው ገንዘብ እንዲገበያዩ እየሠራ ነው፤ ተሳክቶላቸዋልም ነው የሚሉት።

የቻይና፣ የብራዚል እና የሕንድ ኢኮኖሚ ደግሞ ከማንም በማይተናነስ መልኩ ወደፊት እየመጣ መሆኑን የሚጠቁሙት ሸዋፈራው፤ የብሪክስ ሀገራት ሀብት በጥቅል የአሜሪካንን በልጦ በተገኘ ጊዜ የዓለም ፖለቲካዊ የኢኮኖሚ ሥርዓት አቅጣጫውን እንደሚቀይር የሚያመላክቱ ብዙ ነገሮች አሉ ብለዋል።

የብሪክስ ሀገራት የራሳቸውን ገንዘብ አቅም በማሳደግ ዶላርን ዋጋ ለማሳጣት እየጣሩ ነው የሚሉት የፖለቲካል ኢኮኖሚ ተንታኙ፤ ወደፊት የኃይል አሰላለፍ ለውጥ መኖሩ አይቀሬ ይመስላል። ኢትዮጵያም ከሚለወጠው ዓለም ጋር ተወዳዳሪ ሆና ለመዝለቅና ድርሻዋን ማግኘት እንድንችል የቤት ሥራዎን ቀድማ ማገባደድ ይኖርባታል ሲሉ አሳስበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የተገኙ ውጤቶች ተጠናክረው ይቀጥሉ!

መንግሥት ሐምሌ 22 ቀን 2106 ዓ/ም ኢትዮጵያ ወደ ተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ መግባቷን ይፋ ካደረገበት ወቅት አንስቶ በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ ጎኑ በርካታ አስተያየቶች ሲሰጡ ቆይተዋል። አንዳንዶች እንዲያውም ዘግይቷል ሲሉ ሌሎች ኢትዮጵያ ከእንግዲህ ወዲያ ‹‹አበቃላት›› የሚል አስተያየትም እስከመስጠትም ደርሰው ነበር። ሆኖም ባለፉት ሦስት ወራት የታየው ግን ከዚህ በእጅጉ የተለየ እና የማክሮ ኢኮኖሚው ማሻሻያው ቀደም ብሎ መተግበር ይገባው እንደነበር ያሳየ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ለረጅም ዘመን ስትፈተንባቸው ከቆየችባቸው ተግዳሮቶች ውስጥ የመጠባበቂያ ገንዘብ እጥረት አንዱ ነው። ለዘመናት ያህል በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ውስጥ የነበረው የመጠባበቂያ የውጭ ምንዛሪ የሳሳ የነበረ ከመሆኑም በላይ ሀገሪቱ ችግር ቢገጥማት ፈተናውን እንዴት ትወጣው ይሆን የሚል ስጋትን ሲጭር የቆየ ነው፡፡

የማክሮ ኢኮኖሚው ማሻሻያው ተግባራዊ መደረግ ከጀመረ በኋላ የሀገሪቱ የመጠባበቂያ ገንዘብ ክምችት በከፍተኛ መልኩ ለውጥ አምጥቷል። ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ለክፉ ቀን ብላ የምታስቀምጠው የመጠባበቂያ ገንዘብ ባለፉት ሦስት ወራት 161 በመቶ አድጓል፡፡ የግል ባንኮች ሪዘርብ በ29 በመቶ አድጓል። ይህም ለዘመናት በስጋትነት ሲነሳ የነበረውን የሀገሪቱን የመጠባበቂያ ገንዘብ ክምችት አስተማማኝ በሆነ መልኩ እየተፈታ መሄዱን የሚያመላክት ነው፡፡

በገቢ ረገድ የታየውም እመርታ የማክሮ ኢኮኖሚው ማሻሻያው ውጤታማነትን ያሳየ ነው። የማክሮ ኢኮኖሚው ማሻሻያው ኮንትሮባንድን እና የታክስ ስወራን በእጅጉ በመቀነስ ሀገራዊ ገቢን እያሳደገ ነው። ባለፉት ሦስት ወራት 180 ቢሊዮን ብር ገቢ ተሰብስቧል። ዘንድሮ በሦስት ወራት ብቻ የተሰበሰበው ገቢ በ2010 ከገባው 176 ቢሊዮን ብር ዓመታዊ ገቢ የላቀ ነው። የማክሮ ኢኮኖሚው በፈጠረው ምቹ ሁኔታም ዘንድሮ 1 ነጥብ 5 ትሪሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዷል። ያለፉት ሦስት ወራት አፈጻጸም የሚያሳየውም የታያዘው ዕቅድ እንደሚሳካ ነው፡፡

በተመሳሳይም የኢኮኖሚ ማሻሻያው ከኤክስፖርት የሚገኘውን ገቢ ከፍተኛ በሆነ መልኩ እንዲጨምር አድርጎታል። ባለፉት ሦስት ወራት ብቻ 1 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር ገቢ የተገኘ ሲሆን ይህም አፈጻጸም ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ ነው። ይህም አፈጻጸም ሀገሪቱ በዚህ ዓመት ከ5 ቢሊዮን ዶላር በላይ ማግኘት እንደምትችል የሚያሳይ ነው። ይህም ለኢትዮጵያ አዲስ ታሪክ ነው፡፡

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ኮንትሮባንድ እና ብልሹ አሠራሮችን በመከላከል አዎንታዊ ሚና እየተጫወተ በመሆኑ ወርቅን የመሳሰሉ በኮንትሮባንድ ይወጡ የነበሩ ምርቶች ከፍተኛ ገቢ እንዲያስገቡ አድርጓቸዋል። ባለፉት ሦስት ወራትም ወርቅ 500 ሚሊዮን ዶላር ያስገባ ሲሆን ይህም ወርቅ ወደ ውጭ ከተላኩ ምርቶች በገቢ የመጀመሪያውን ደረጃ እንዲይዝ አድርጎታል፡፡

በማክሮ ኢኮኖሚው ማሻሻያው ምክንያት ከውጭ የሚላክ የገንዘብ መጠን ወይም ሬሚታንስም ጨምሯል። ከውጪ ወደሀገር ውስጥ የሚገባው የሬሚታንስ ገቢ ባለፉት 3 ወራት 24 በመቶ ዕድገት ተመዝግቦበታል። ይህም በውጭ ሀገር የሚገኙ ዜጎች በኢትዮጵያ እየተተገበረ ያለው የኢኮኖሚ ሪፎርም ገንዘባቸውን በቀጥታ በሕጋዊ መልኩ በባንክ እንዲልኩ ምቹ ሁኔታ እንደፈጠረላቸው እና በሀገራቸው ኢኮኖሚ ውስጥ አዎንታዊ አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ ዕድል እንደፈጠረላቸው የሚያመላክት ነው፡፡

በሌላ በኩል የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው በሀገር ውስጥ ተተኪ ምርቶች እንዲበራከቱ እና ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች እንዲቀንሱ በማድረግ ረገድ አዎንታዊ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል። ባለፉት ሦስት ወራትም ከውጭ የሚገቡ ዕቃዎች በ1 ነጥብ 3 በመቶ ቀንሰዋል። በምትኩም የሀገር ውስጥ ምርቶች ተፈላጊነት ጨምሯል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት እውነታዎች በአጠቃላይ ኢትዮጵያ የተገበረችው የተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ጉልህ የሆኑ ለውጦችን እያመጣ መሆኑን ባለፉት ሦስት ወራት የተገኙት ውጤቶች ምስክር የሚሆኑ ናቸው። ስለዚህም የተጀመረው የለውጥ እንቅስቃሴ ተጠናክሮ ሊቀጥል እና የታየውን የኢኮኖሚ ማንሰራራት ወደ ተሟላ ብልፅግና ማድረስ ይገባል!

**አዲስ ዘመን**
ኢፕድ
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## እግር ኳሱን ከወደቀበት ለማንሳት…

ማሕሌት ጋሻው

ከዓመት ዓመት ከትልልቅ የአሕጉሪቱ የውድድር መድረኮች እየራቀ የመጣው የኢትዮጵያ እግር ኳስ ከመሻሻል ይልቅ እየተዳከመ እንደመጣ የአደባባይ ምስጢር ነው። ለዚህ እንደምክንያት የሚጠቀሱ ብዙ ተግዳሮቶች አሉ። ከነዚህም መካከል ጠንካራ አመራር ማጣት፣ ስፖርቱ ከባለሙያዎች እጅ ወጥቶ ጥቅም በሚያሳድዱ ግለሰቦች እጅ መውደቅ፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ችግር፣ የታዳጊዎች እግር ኳስ ፕሮጀክቶች ውጤት አልባ መሆን ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛሉ። እነዚህ ምክንያቶች ለኢትዮጵያ እግር ኳስ እድገት ማነቆ ሆነው የቁልቁለት ጉዞውን የሚያፋጥኑ ጉዳዮች እንደሆኑም የዘርፉ ባለሙያዎች ያነሳሉ።

የኢትዮጵያ የእግር ኳስ ችግር ሰፊ እና ዘርፈ ብዙ ቢሆንም በመንግሥት ደረጃ ቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቶት መሠራት ይኖርበታል። በተለይም በዚህ ወቅት ኢትዮጵያ የ2029 የአፍሪካ ዋንጫን የማዘጋጀት ጥያቄ እንደማቅረቧ ከወዲሁ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

የእግር ኳሱን ተረካቢና ተተኪዎች ለማፍራት ታዳጊዎች ላይ መሥራት እንደሚገባ ብዙ ጊዜ ሲነሳ ቆይቷል። ከክለቦች ውጤት አልባ አሕጉራዊ ተሳትፎ አልፎ በብሔራዊ ቡድን ደረጃ ለሚታየው የውጤት ማሽቆልቆል፣ በተሰጥዖ፣ ቴክኒክና ታክቲክ እንዲሁም በአካል ብቃት የዳበሩ ታዳጊ እግር ኳስ ተጫዋቾችን ማፍራት አለመቻሉ ዋነኛው ችግር በመሆኑ ሊጤን ይገባል።

የኢትዮጵያን ብሔራዊ ቡድን ከ31 ዓመታት በኋላ ለአፍሪካ ዋንጫ ያበቁት አሠልጣኝ ሰውነት ቢሻው በአንድ ወቅት እንደተናገሩት፣ የእግር ኳሱን እድገት የጎተቱትን ችግሮች ለመቅረፍ ሰፊ ጥናትና ምርምር እንደሚያስፈልግና ታዳጊዎች ላይ መሥራት እንዳለበት ተናግረው ነበር። አሠልጣኙ በብሔራዊ ቡድን የሠሩትን ታሪክ ለመድገም እና የኢትዮጵያን እግር ኳስ ለማከም፣ የታዳጊ እግር ኳስ ፕሮጀክት ከፍተው እየሠሩም ይገኛሉ፡፡

በፕሮጀክቶች አልፈው በማሠልጠኛ ማዕከላት እና አካዳሚዎች ሠልጥነው በትክክለኛው እድሜ የሚወጡ ስፖርተኞች ለዘመናዊ እግር ኳስ የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች የመያዝ ዕድል አላቸው። በሀገራችን ያለው እውነታ ግን ከዚህ በተቃራኒ ነው። ከክለብ አልፈው በብሔራዊ ቡድንም ጭምር የሚጫወቱት አብዛኞቹ ተጫዋቾች እግር ኳስን የሚጫወቱት በራሳቸው ተነሳሽነት እና በልምድ ነው። ይህም ሊሆን የቻለው ከታዳጊነት እድሜ ጀምረው፣ በእውቀት የተደገፈ እንዲሁም ሳይንሳዊና መሠረታዊ የእግር ኳስ ሥልጠናዎችን ማግኘት ባለመቻላቸው ነው። በሳይንሳዊ መንገድ የተደገፈ ሥልጠናን በተገቢው እድሜ የሚያገኙ ቢሆን እግር ኳሱን አንድ ደረጃ ከፍ የሚያደርግና ኢትዮጵያን በዓለም ተፎካካሪ ማድረግ የሚችል አቅም እንዳለ ግን የሚካድ አይደለም፡፡

> **የኢትዮጵያ እግር ኳስ ከልማዳዊ አሠራር ወጥቶ ዘመኑ የሚፈልገውን አሠራር መዘርጋትና የእግር ኳሱን እድገት የሚያፋጥኑ መንገዶችን መከተል ይኖርበታል**

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ከልማዳዊ አሠራር ወጥቶ ዘመኑ የሚፈልገውን አሠራር መዘርጋትና የእግር ኳሱን እድገት የሚያፋጥኑ መንገዶችን መከተል ይኖርበታል። ከላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች በሙሉ እንደየደረጃቸው ለውጤት ማሽቆልቆል ሚና ቢኖራቸውም ትልቁን ስፍራ የሚይዘው የአሠራር ሥርዓት ነውና በቶሎ መፍትሔ ሊሰጠው ይገባል። የተበላሸና የትም የማያደርስ የእግር ኳስ ሥርዓት ይዞ የተቀሩት ችግሮች ላይ መሥራት ፈታኝ በመሆኑ ከመዋቅር ጀምሮ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን መፈተሽ ለነገ የሚባል አይደለም።

አሁን ላይ በዓለም ስመ ጥር የሆኑት የእግር ኳስ ከዋክብቶች ከታዳጊነታቸው አንስቶ በጥሩ የእግር ኳስ ሥርዓት ውስጥ አልፈው ውጤታማ መሆናቸው እውን ነው። እኛም ታዳጊዎች ላይ ስር ነቀል የሆነ ሥራን በመሥራት የስፖርት ቤተሰቡ የሚናፍቀውን የእግር ኳስ ውጤት ለመመለስ መሥራት ይኖርብናል፡፡

የዓለም እግር ኳስ አሁን ላለበት ደረጃ የደረሰው ሀገራት በዘረጉት ምቹ አሠራር እና ታዳጊዎች ላይ ሰፊና ቀጣይነት ያለው ሥራ በመሠራቱ እንደሆነ የሚታይ ሐቅ ነው። የእግር ኳስ ተሰጥዖ ያላቸው ታዳጊዎችን በሳይንሳዊ እውቀት አስደግፎና ያላቸውን ክህሎት የሚያጎለብቱ የእግር ኳስ ፕሮጀክቶችን ለመፍጠር መረባረብ ይኖርብናል።

እግር ኳስ ክለቦች የራሳቸው የሆነ የታዳጊ ልማትን በተገቢው ሁኔታ አለመያዛቸውና ቢይዙም በክትትል ችሎታቸው ላቅ ያሉ ተጫዋቾችን ለማፍራት ሲቸገሩ እየታየ ነው። በመንግሥትም በኩል የተከፈቱ ፕሮጀክቶች የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት አልቻሉም። በየእድሜ ደረጃው ታዳጊዎች ላይ የሚሠሩ ጥቂት ክለቦች ቢኖሩም ደፍረው ዕድል በመስጠትና በማሳደግ ረገድ ግን ብዙ ርቀት አይጓዙም።

በኢትዮጵያም በተለያዩ የእድሜ እርከኖች ባሉት ታዳጊዎች ላይ ምልመላ በማድረግ የሚያሠለጥኑ የቀድሞ የእግር ኳስ ተጫዋቾች ብቅ ብቅ እያሉ ይገኛሉ። በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን እንዲሁም በኢትዮጵያ ቡና ድንቅ ጊዜን ማሳለፍ የቻለው የመሐል ሜዳ ተጫዋቹ ዳዊት እስጢፋኖስ እድሜያቸው ከአምስት እስከ አስራ አምስት የሆኑ ታዳጊዎችን እና በስሩ አራት የሚሆኑ አሠልጣኞችን ይዞ ለመጪው የኢትዮጵያ እግር ኳስ ግብዓት የሚሆኑ ታዳጊዎችን ለማፍራት ከሚንቀሳቀሱት ውስጥ ተጠቃሽ ነው።

ልክ እንደ ዳዊት የኢትዮጵያ እግር ኳስ ከወደቀበት ተነስቶ እንዲያድግ ዝቅ ብለው ታዳጊዎች ላይ መሥራት ያለባቸው ብዙ ባለሙያዎች አሉ። ያም ሆኖ ይህ የቤት ሥራ በግለሰቦች ላይ ብቻ የሚጣል አይደለም።ከፌዴሬሽን በተጨማሪ መንግሥትም ለችግሩ ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ በቅርብ ክትትል መሥራት አለበት።

በታዳጊዎች ትክክለኛ እድሜ ላይ በንቃት በመሥራት ረገድ ክለቦች ያሉባቸውን በርካታ ችግሮች ቀርፈው በትክክለኛው ሐዲድ ላይ ሊጓዙ ይገባል። ክለቦች የሚታየውን ችግር መቅረፍ ብቻ ሳይሆን ያለፉባቸው ታዳጊዎች ዕድል እንዲያገኙ ማድረግ ላይ ሊያተኩሩ ይገባል። በዚህ ረገድ በጣት የሚቆጠሩ ክለቦች በየጊዜው ታዳጊዎችን ወደ ዋናው ቡድን ለማሳደግ የሚያደርጉት ጥረት ሊደነቅ ይገባል። ሌሎችም በርካታ ክለቦች ረብጣ ገንዘብ እያወጡ ተጫዋቾች ከመግዛት ይልቅ ፊታቸውን ወደ ታዳጊዎች ሊመልሱ ይገባል።

ሌላው የእግር ኳሱ ዋነኛ ችግር የማዘውተሪያ ስፍራዎች እጥረት መሆኑ ይታወቃል። ይህ ችግር በተለይም ለታዳጊዎች ሥልጠና ፈተና መሆኑ በተደጋጋሚ ሲነገር ቆይቷል። በዚህ ምክንያት በተለያዩ የእድሜ እርከኖች ታዳጊዎችን ለይቶ ለማሠልጠን እንዳልቻሉም ባለሙያዎች ዘወትር ቅሬታ ያቀርባሉ። እንደ ችግሩ ስፋት እና ግዝፈትም ሊሰጠው የሚገባው ትኩረት አልተሰጠውም።

በቅርብ ጊዜ ይሄን ችግር ለመፍታት በመዲናዋ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አነሳሽነት፣ የተሠሩ ትናንሽ የእግር ኳስ ሜዳዎች ቢኖሩም፣ ከከተማው ነዋሪ ቁጥር አንፃር እዚህ ግባ የሚባሉ አይደሉም። ስለዚህም ከመንግሥት በተጨማሪ ባለሀብቶችም በየአካባቢያቸው የማዘውተሪያ ስፍራዎችን በመገንባት ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን በመወጣት ለእግር ካሱ ትንሳዔ የራሳቸውን ዐሻራ ሊያሳርፉ ይገባል፡፡

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

## ነፃ ሃሳብ

# የኃይል አማራጭን የሚፀየፍ ትውልድና አገር ለመገንባት

ሰው መሆን

የሕዝብ እንደራሴዎች በተወካዮች ምክር ቤት ተሰይመዋል። ስለ አገራዊ፣ ቀጣናዊና ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች እያነሱ ጥያቄዎችን ያቀርባሉ። በምክር ቤቱ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተገኝተዋል። ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ማስታወሻ ይይዛሉ። በዚህ መሃል ነው ሰላምን የተመለከቱ ርዕሰ ጉዳዮች መንሸራሸር የጀመሩት።

አንድ ከደቡብ ክልል ጋሞ ዞን የቁጫ ብሔረሰብ የወከሉ የምክር ቤቱ አባል ጥያቄዎቻቸውን ማቅረብ ጀመሩ። ዜጎች መብቶቻቸውን በመጠየቃቸው፣ ባህል ወጋቸውን በመከተላቸው፤ እራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር በመፈለጋቸው ምክንያት በምላሹ ድምፃቸው እንደታፈነ፣ ሰዎች በፀጥታ ኃይሎች እንደተገደሉ የተለያዩ ወከባ እንደሚደርስባቸው እና ሌሎችም ጉዳዮችን በማጣቀስ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ አቤት አሉ።

በመቀጠል የዘይሴ ብሔረሰብ የወከሉ የምክር ቤት አባል እንዲሁ ተመሳሳይ ጥያቄ አስከተሉ። የወከሉት ሕዝብ እራሱን በራሱ ለማስተዳደር ጥያቄ ቢያቀርብም በምላሹ ግጭት፣ መፈናቀል፣ ግድያ እና ሌሎችም መሰል ችግሮች እየገጠሙት እንደሆነ አነሱ። በአካባቢው ሰላም አለመኖሩን የፀጥታ ኃይሎች በሕዝቡ ላይ በደል እያደረሱ መሆኑን ጠቁመው የፌደራል መንግስት እልባት እንዲሰጣቸው ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥያቄያቸውን አቀረቡ።

የሁለቱ ብሔረሰቦች ተወካዮች ያነሱትን ቅሬታ ተቃውመው ግጭቱን ከማርገብ ይልቅ በእሳት ላይ ጋዝ እየጨመሩ ነው የሚል ሌላ ተቃውሞ ከአንድ የምክር ቤት አባል ተነስቶ ነበር። የቀረቡት አሳሳች መረጃዎች ለሰላም መፍትሄ ሳይሆኑ ግጭትን ይበልጥ የሚያባብሱና በውስጣቸው ሴራ የያዙ መሆኑንም በመግለፅ ቅሬታቸውን አቅርበዋል። ተወካዮቹ ሕዝብን አወያይቶ ሰላም ለማምጣት ቁርጠኝነት እንዳልነበራቸውና የወከላቸውን ማህበረሰብ ኃላፊነት እንዳልተወጡ በመጥቀስ በቸልተኝነት ክስ ቀርቦባቸዋል።

በሌላ በኩል ከአማራ ክልል የተወከሉ የምክር ቤቱ አንድ አባል በበኩላቸው የመጡበትን ክልል ጨምሮ በልዩ ልዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ግጭት፣ ጦርነት፣ መፈናቀል እና ሞት፣ በሴቶች ላይ የሚደርስ ፆታዊ ጥቃት እንዲሁም የሰብዓዊ መብት ጥሰት የአገሪቱን ሰላም ማደፍረሱን፣ ኢኮኖሚውን ማድቀቁን፣ ዜጎች ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰው ለመስራት እንዳይችሉ መገደቡን በማንሳት መንግስት የሰላም ባንዲራን በማውለብለብ ሆደ ሰፊነቱን እንዲያሳይ፣ ከታጣቂዎች ጋር ለመደራደር ለምን አይሞክርም የሚል ጥያቄን አስከተሉ። መንግስት የኃይል አማራጭን ወደጎን ትቶ ትጥቅ ካነገቡ ኃይሎች ጋር ለመደራደር ያለው ቁርጠኝነትን ጠየቁ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩም በእነዚህ ጉዳዮች ላይ በቂ ማብራሪያ መስጠታቸውን በወቅቱ በቀጥታ የቴሌቪዥን ጣቢያ የተላለፈውን የምክር ቤቱ ስብሰባ ስንከታተል ሰምተናል። መንግስታቸው በአገሪቱ የሰላም አየር እንዲሰፍን ፍፁም ቁርጠኛ መሆናቸውን ያሳዩ ምላሾችና መሬት የተከሰተውን እውነታ ገላልጠው ሲያስረዱ አድምጠናል። የሰላም እጦት የአገሪቱን እድገት አንዴት አንደጎዳው፣ ግጭት፣ የትጥቅ ትግል ምን ያህል ወደ ኋላ እንዳስቀረን በዝርዝር ተናግረዋል።

መንግስታቸው ዛሬም ነገም የውስጥ ችግሮችን ለመፍታት ሰላማዊ አማራጭን እንደሚከተልና በዚያም ፍፁም እንደሚያምን አብራርተዋል።

**ፖለቲከኞች የትኛውንም አይነት የፍትሀዊነት፣ የዲሞክራሲ፣ የኢኮኖሚ የፖለቲካ ውክልና ጥያቄዎችን በተመለከተ መፍትሄ ለመስጠት የሰላሙን መንገድ መከተል ይኖርበታል**

ረዘም ያሉ ዘመናትን በትጥቅ ትግል ውስጥ ያሳለፉ ኃይሎች እራሳቸውንም፣ ሕዝቡንም አገሪቱንም ከመጉዳት ያለፈ የፈየዱት አንዳች እንኳን አለመኖሩን በማንሳት ወደ ሰላሙ መንገድ እንዲመጡና በጠረጴዛ ዙሪያ ችግሮችን በጋራ ለመፍታት እንዲመክሩ ገልፀዋል።

የዚህ ፅሁፍ አዘጋጅ እነዚህ ጉዳዮችን በወቅቱ በጥሞና ሲከታተል ነበር። ለዚህም ነው ከዚህ የሚከተሉትን ጉዳዮች በቅንነትና ፍፁም መፍትሄን በሚሻ አንደበት በዝርዝር ምልከታውን ለማስቀመጥ የወደደው። እርግጥ ነው አባቶቻችን ‹‹እሳት በሌለበት ጭስ አይታይም›› ይላሉ። በምክር ቤት የተነሱ የሰላም እጦት ችግር በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የሉም፤ ጥያቄዎቹም መሰረት የላቸውም ብሎ መካድ አይቻልም። ግችሩ መሬት ላይ አለ። በተለያዩ ግዜያት ከሰላማዊ መንገድ የተለየ እሳቤን የያዙ ኃይሎች ስርዓትን ለማፍረስ፣ ማህበረሰብን እረፍት ለመንሳት ነፍጣቸውን መዝዘዋል። በውጤቱ ሰዎች ሞተዋል አሁንም እየሞቱ ነው። ሀብት ንብረት ወድሟል፤ አሁንም እየወደመ ነው። ዜጎች ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀሱ ይታገታሉ፤ አሁንም ይህ ስጋት እንዳለ ነው። ዜጎችን በማንነት፣ በክልል፣ ወረዳ፣ ልዩ ወረዳ አደረጃጀት ስም በመቀስቀስ ወደ ግጭት የሚከቱ አካሄዶችን የሚከተሉ በርካቶች ናቸው።

ሕዝብን እንወክላለን ያሉና ፖለቲካዊ መፍትሄ የሚሰጥ አጀንዳ እንዳላቸው የሚናገሩ አካላት፤ ከሰላም ይልቅ ግጭትን፤ ከጠረጴዛ ይልቅ ምሽግን ምርጫቸው አድርገዋል። ለመሆኑ ይህ አካሄድ ምን ያህል ያዋጣል? ለሕዝቡ ወጥቶ መግባት፣ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት መጠንከር ምን ያህል ጠቃሚ ነው? እኛ በጎጥ፣ ዘር እና በሌሎች በቀላል ውይይት ሊፈቱ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ እሳት ስንጭር ዓለም በስልጣኔ፣ በእድገትና በዘመናዊነት እሩቅ ጥሎን እንደሄደ እንዴት ማወቅ ተሳነን? በቂ ችግር፣ በቂ ጠላት እያለን ነግቶ በመሸ ቁጥር እርስ በእርስ የሚያጋጩና የሚያባሉ ችግሮችን እየፈለፈልን የምናድረው ለምን ይሆን?

እነዚህ ጠያቄዎች ፍፁም ቅን ምላሽ ይፈልጋሉ። የዚህ ፅሁፍ አዘጋጅ ግን ጥያቄዎቹ ከቅንነት የተለየ የረቀቀ ሳይንሳዊ ምርምር የሚፈልጉ ከባድ ችግሮች አለመሆናቸውን ያምናል። ፖለቲከኞች የትኛውንም አይነት የፍትሀዊነት፣ የዲሞክራሲ፣ የኢኮኖሚ የፖለቲካ ውክልና ጥያቄዎችን በተመለከተ መፍትሄ ለመስጠት የሰላሙን መንገድ መከተል ይኖርበታል።

እነዚህ አጀንዳዎች የግለሰቦችን፣ የማህበረሰብን በጥቅሉ የአገርን ሰላም ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል። ከነፍጥ ይልቅ፣ ጠረጴዛን ምርጫ ማድረግ ይገባናል። በመንግስት በኩል የሰላም ፍላጎት መኖሩን እየተመለከትን ነው። ነፍጥ ያነገቡትን ብቻ ሳይሆን፣ የማንነትና የአደረጃጀት ጥያቄዎችን ከሚያነሱ አካላት ጋር ሕጋዊና ሰላማዊ አካሄድን ለመከተል መንግስት እረጅም እርቀት እየተጓዘ ነው። ይህ ሆደ ሰፊነትን ያሳያል። በምክር ቤት ውስጥ የሰላምን ፍፁም አስፈላጊነትና የመንግስታቸውን ቀና ሀሳብ መሰረት አድርገው ምላሽ የሰጡት ጠቅላይ ሚኒስትሩም ይህንኑ ሀሳብ ነው አበክረው ሲያነሱ ያደመጥነው።

‹‹መንግስት ለሰላም ምን ያህል ቁርጠኛ ነው። ለድርድርና ለመነጋገርስ ምን ያህል ተዘጋጅቷል›› በሚል ለተነሳው ቅን ጥያቄ በጎ ምላሽ አድምጠናል። ‹‹ከቻላችሁ እናንተም ቢሆን የማደራደር ኃላፊነቱን መውሰድ ትችላላችሁ እኛ ዝግጁ ነን›› የሚል ምላሽ እስከመስጠት የደረሰ ዝግጁነት መኖሩን ተመልክተናል። በመንግስት በኩል ይህንን ያህል ዝግጁነት ካለ፣ ማንኛውንም ጥያቄ ከኃይል ይልቅ በሰላም ለመፈታት የሚያስችል ሆደሰፊነት ከታየ ነፍጥን፣ ግጭትን ምርጫቸው ያደረጉ አካላት ምን ምክንያት ኖሯቸው ነው ወደ ሰላሙ መድረክ ለመምጣት ያልደፈሩት?

ዜጎች ይህንን ጥያቄ ደጋግመው ማንሳት ይኖርባቸዋል። ኃይልን ምርጫ ያደረጉ ኃይሎች (በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል የሚገኙ) ወደ ሰላም መድረክ እንዲመጡ ግፊት ማድረግ ይኖርበታል። ምክንያቱም ከዚህ የባሱ በርካታ የቤት ስራዎች አሉብን። አገራችንን ከኋላ ቀርነት የሚያላቅቁ የልማት ፕሮጀክቶች ላይ መሳተፍ ይኖርብናል። ከዓለም አገራት ጭራ ሳይሆን ፊት መቀመጥ ይኖርብናል። በቃጣናው እድገታችንን የሚፃረሩ፣ አንድነታችንን የሚጠሉ ኃይሎች እየተፈጠሩ ነው። የውስጥ ችግራችን ላይ ጋዝ የሚያርከፈክፉና በፍርስራሻችን ላይ የበላይነታቸውን ለመገንባት የሚታትሩ ዙሪያችንን ከበውናል። ለዚህ በራችን ክፍት መሆን አይጠበቅበትም።

ሰላምን ምርጫ ማድረግ ያለብን ጠላቶቻችን ሰለከበቡንም ብቻ አይደለም። የሰላም መንገድ፣ የውይይትና የምክክር አማራጭ ለፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ሌሎች አያሌ ችግሮቻችን መከተል የሚኖርብን ሕዝባችን ይህ ስለሚገባው ነው። ኑሮውን ለማሻሻል ከሰላም በላይ ሌላ ምንም ስለማያስፈልገው ነው። አርሶ፣ ነግዶና ሸምቶ ኑሮውን ለመምራት ቅድሚያ ሰላምን ይሻል።

እርግጥ ነው ዲሞክራሲያዊ መብቱን ተጠቅሞ ማህበረሰቡ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ እኩልነት ተጠቃሚ መሆን አለበት። ሰብዓዊ መብቶቹ መጠበቅ ይኖርበታል። እራሱን በራሱ በመረጠውና በድምፁ በወከለው አካል ሊተዳደር ይገባል። እነዚህን መብቶቹን እናስጠብቃለን የሚሉ ፖለቲከኞች እና ግለሰቦች ግን ውይይትን፣ ድርድርን ሰላማዊ የፖለቲካ ትግልን መከተል ይኖርባቸዋል።

በዚህ ምክንያት ነው መንግስት በከፈተው የፖለቲካና የድርድር ምህዳሮች ውስጥ በሁሉም የአገሪቱ አካባቢ ያሉ ልዩነት ያላቸው ኃይሎች መሳተፍ የሚኖርባቸው። ጥያቄዎችን አጀንዳ ለማድረግ እና ቅድሚያ ተሰጥቷቸው በዲሞክራሲያዊ መንገድ፣ በድርድር (በሰጥቶ መቀበል መርህ) ዘላቂ እልባት እንዲያገኙ ዝግጁ መሆን አለባቸው።

የሕዝብ እንደራሴዎች በምክር ቤቱ ውስጥ የወከሉትን ማህበረሰብን ድምፅ ማሰማታቸውና ቅሬታቸውን ለመንግስት ማቅረባቸው አንዳች ስህተት የለበትም። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልጣን በያዙበት ወቅት ሁሉም ድምፆች እና የልዩነት ሀሳቦች በምክር ቤቱ ውስጥ በዲሞክራሲያዊና ሰላማዊ መንገድ ሊሰሙ እንደሚገባ ቃል ገብተዋል። እነዚህ ድምፆች በእርግጥም እየተሰሙ ነው። ይሁን እንጂ ይህንን መንገድ ለቅቀው ነፍጥን ያነገቡ ኃይሎች አሉ። መንግስት አሁንም እነዚህ ኃይሎች ወደ መሰል የሰላም መድረኮች መጥተው ጥያቄዎቻቸውን በሰላምና በድርድር እንዲፈቱ በብሔራዊ ቴሌቪዥን ቀጥታ በሚተላለፍ መልእክት ጭምር ጥሪ እያስተላለፉ ነው። ለዚህ ነው የተከፈተውን ምህዳር መጠቀሙ ለሁሉም ወገን የሚበጅ እንደሆነ ለመግለፅ የምወደው።

እዚህ ጋር አንድ ጉዳይ ትኩረት ማግኘት እንዳለበት አምናለሁ። እርሱም ሕዝባቸውን ወክልው በምክር ቤቱ ውስጥ በዲሞክራሲያዊ መንገድ ጥያቀዎችን የሚያቀርቡ፣ ችግሮች መፍትሄ እንዲያገኙ የሚሞግቱ አካላት ተጨማሪ ኃላፊነት መውሰድ ይጠበቅባቸዋል። የመጡበት ማህበረሰብ አካባቢ ለሚኖር ማንኛውም ከሰላም ያፈነገጠ፣ ግጭትን ምርጫው ያደረገ ኃይል ወደ ዲሞክራሲያዊ የሰላም አማራጮች እንዲመጣ ግፊት የማድረግ ኃላፊነት ሊወስዱ ይገባል። የወከሉትን ሕዝብ በማወያየት ግጭትን አማራጭ ያደረጉ ቡድኖች ወደ ሰላማዊ ድርድር እና ውይይት እንዲመጡ መስራት አለባቸው።

ከሰሞኑ በተካሄደው የሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት የሰማናቸው ልዩ ልዩ ድምፆች የሚያመለክቱት ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ለመገንባት በመንገድ ላይ መሆናችንን ነው። ይህ ሙሉ የሚሆነው ግን ሁሉም አካላት ሰላማዊ መንገድ ሲከተሉ ብቻ ነው። ‹‹በጥባጭ ካለ ማን ጥሩ ይጠጣል›› እንዲሉ በሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች ለሚነሱ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የፍትህ ጥያቄዎች ሁሉም አካላት ሰለማዊ መድረኮችን የመጠቀም ፍላጎት ሊኖራቸው ይገባል። ይህ ከሌላቸው እየታየ ያለው የዲሞክራሲ ጭላንጭሉ መክሰሙ የማይቀር ነው። በዚህ ምክንያት የአገሪቱን ሰላም ለማስፈን፣ ዘላቂ እድገት ለማረጋገጥ፣ በቀጠናው ታላቅ ኃይል ሆኖ ለመውጣት፣ በዓለም የፖለቲካ ኢኮኖሚ ላይ ከልዕለ ኃያላኖቹ ጋር ለመስተካከል የውስጥ ሰላማችንን እና የቤት ስራችንን በአግባቡ እልባት መስጠት እንዳለብን አምናለሁ። ሰላም !!

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የቁልፍ መሠረተ ልማቶችን የሳይበር ደህንነት ለመጠበቅ

**ወርቅነሽ ደምሰው**

በዓለም አቀፍ ደረጃ የሳይበር ደህንነት ስጋት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን ተከትሎ የሳይበር ጥቃቶች እየተበራከቱ አሳሳቢ ሁኔታዎች እየተፈጠሩ ይገኛሉ። ከሚሰነዘሩት የሳይበር ጥቃቶች ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙት ደግሞ በቁልፍ መሠረተ ልማቶች ላይ የሚደረጉት መሆናቸውንም መረጃዎች ይጠቁማሉ።

መረጃዎቹ እንደሚያመላክቱት፤ በቁልፍ መሰረተ ልማቶች ላይ የተቃጡ ጥቃቶች ብዙ ችግሮችን ያስከትላሉ። ለአብነት እ.ኤ.አ.በ2021 በአሜሪካ የኮሎኒያል የነዳጅ ማስተላለፊያ መስመር ላይ የተፈፀመው የሳይበር ጥቃት ከፍተኛ የነዳጅ እጥረት ከማስከተሉ ባሻገር የሳይበር ጥቃት መሰረታዊ አገልግሎቶችን እንዴት ማስተጓጎል እንደሚችሉ ያሳየ ክስተት ሆኗል።

በኢትዮጵያም የሳይበር ጥቃት ሙከራው እየጨመረ መምጣቱን መረጃዎች ያመላክታሉ። ባለፈው ዓመት ከተከሰቱ 8ሺ854 የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች መካከል ከፍተኛው ድርሻ የሚይዘው በቁልፍ መሰረተ ልማቶች ላይ የተሞከሩት ናቸው። ይህም አብዛኞዎቹ የሳይበር ጥቃቶች የሚያነጣጥሩት ቁልፍ መሠረተ ልማቶች ላይ መሆኑን ያሳያል።

እነዚህ መረጃዎች እንደ ሀገር የሳይበር ጥቃት ለመመከት የሚያስችል ዝግጅት መደረግ ያለበት ስለመሆኑና ለእዚህ የሚያስፈልጉ ቴክኖሎጂዎችን በመታጠቅ ለቁልፍ መሰረተ ልማቶች ልዩ ጥበቃ ሊደረግ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ።

የጥቅምት ወር ‹‹የሳይበር ደህንነት›› የሚከበርበት እንደመሆኑ የዘንድሮውም የጥቅምት ወር ይህንኑ ታሳቢ ባደረገ መልኩ ‹‹የቁልፍ መሰረተ-ልማት ደህንነት ለዲጂታል ሉዓላዊነት›› በመሪ ሀሳብ እየተከበረ ይገኛል። ይህንኑ ምክንያት በማድረግም የኢትዮጵያን ቁልፍ መሠረተ ልማቶች የሳይበር ደህንነት የሚያስቃኝ የዳሰሳ ጥናት ተሰርቶ ቀርቧል። በጥናቱ ዓለም አቀፍ ተሞክሮ፣ በአገሪቱ ከ2014 እስከ 2016 ዓ.ም በቁልፍ መሠረተ ልማቶች ላይ የተቃጡ ጥቃቶች፣ የተፈጠሩ ክፍተቶች፣ የተወሰዱ እርምጃዎችና የመፍትሔ ሀሳቦች በዝርዝር ተመላክተዋል።

ጥናቱ አቅራቢ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ምክትል ዳይሬክተር አቶ ዳንኤል ጉታ እንዳሉት፤ ቁልፍ መሰረተ ልማቶች ከሀገር ሀገር እንደ ዕድገትና ፍላጎት ደረጃቸው የተለያየ ሊሆን ይችላል። ውስን መሰረተ ልማቶች በሁሉም ሀገራት ቁልፍ ተደርገው ይወሰዳሉ። ሀገራት ያላቸውን የፋይናንስ፣ ቴክኖሎጂና የሰው ኃይል አቅም እንዲሁም የደህንነት ስጋታቸውን ታሳቢ በማድረግ ለተለያዩ ቁልፍ መሰረተ ልማቶች ቅድሚያ ሊሰጡ ይችላሉ።

በዚህ መሠረት አሜሪካና ማላዊን ጨምሮ የ97 ሀገራት ቁልፍ የመሠረተ ልማቶችን ለይተዋል። ቁልፍ ተብለው ከተለዩት መሰረተ ልማቶች ዋና ዋናዎቹ በጤና፣ በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽንና ቴክኖሎጂ፣ በኃይል፣ በጸጥታና ደህንነት፣ በውሃና ፍሳሽ፣ በኢንዱስትሪ፣ በምግብ፣ በትራንስፖርት፣ በፋይናንስ እና በመንግሥት አገልግሎቶች ዘርፎች ናቸው።

የበርካታ ሀገራትን ተሞክሮች የጠቀሱት አቶ ዳንኤል፤ እነዚህን ተሞክሮዎች እንደ ሀገር በመቀመር የጠንካራ ቁልፍ መሰረተ ልማቶችን የሳይበር ደህንነት ማስጠበቅ የሚያስችል ሁሉን አቀፍ አካሄዶች መከተል እንደሚገባ አስገንዝበዋል። በአገሪቱ አሁን እየታየ ካለው ከፍተኛ የሳይበር ስጋት አንፃር ወቅቱን ታሳቢ ያደረገ የሳይበር ደህንነትን የማስጠበቅ ስራ መስራት ወሳኝ መሆኑን አመላክተዋል።

በጥናቱ ቁልፍ መሰረተ ልማቶችን ለመለየት የሚያስችሉ አራት መሰረታዊ መስፈርቶችን ያቀረቡት አቶ ዳንኤል፤ ቁልፍ መሰረተ ልማቶች ለሀገር ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ዕድገት የማይተካ ሚና እንዳላቸውም አመላክተዋል። መሰረተ ልማቶቹ ከአንድ ዘርፍ በላይ የሚያገለግሉ፣ ለሀገር ግንባታ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱና ከፍተኛ መዋለ ነዋይ የሚጠይቁ መሆናቸውን ይገልጻሉ። እነዚህ ተቋማት ላይ ጉዳት ቢደርስ በብሔራዊ ጥቅምና ደህንነት፣



አቶ ዳንኤል ጉታ

እንዲሁም በዜጎች ሕይወት ላይ ከፍተኛ ቀውስ ሊፈጥር እንደሚችል አመላክተዋል።

ለቁልፍ የኢንፎርሜሽን መሠረተ ልማቶች ልዩ ጥበቃ ማድረግ እንደሚያስፈልግ አቶ ዳንኤል አስታውቀው፤ ቁልፍ መሰረተ ልማቶች ለአገርና ለማህበረሰብ ቀጣይነትና መልካም መስተጋብር ያላቸው ሚና ተኪ እንደሌለው ተናግረዋል። ከሚፈጠሩ አሉታዊ ተጽዕኖዎች አንጻር የባላንጣ ሀገራትና የውስጥና ውጭ ጥፋት ኃይሎች ኢላማ መሆን፣ በመሰረተ ልማቶቹ ጥቃቶችና በሀገር ጥቅምና ደህንነት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚፈጥሩና በአንድ ዘርፍ ብቻ ተወስነው የማይቆሙ የመዛመት አቅማቸው ከፍተኛ የሚፈጥሩ መሆናቸውን ገልጸዋል።

አቶ ዳንኤል እንዳሉት፤ ጥናት ማካሄድ ያስፈለገበት ዋንኛ ምክንያት እንደ ሀገር በቁልፍ መሰረተ ልማቶች ላይ የሳይበር ደህነነት ስጋቶች ከምን ጊዜውም በላይ እየጨመሩ በመምጣታቸው ነው። የቁልፍ መሰረተ ልማቶችን ደህንነት የማስጠበቅ ኃላፊነት በውስን አካላት ላይ ብቻ መጣሉ፣ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ኢንሼቲቮች ቀጣይነት ማረጋገጥ የሚያስችል አስገዳጅ የጥበቃ ስርዓት በመዘርጋት ሀገራዊ ዝግጁነት መፍጠር፣ የሳይበር ደህንነት ክስተቶችን በአግባቡ ለማስተናገድና ጉዳታቸውን ለመቀነስ የሚያስችል አስገዳጅ ስርዓት መዘርጋት፣ ሀገራዊ ማሕቀፎችን ከማስፈፀም እና የአቅም ፍተሻና ግምገማ ለማድረግ የሚያስችል አስገዳጅ የቁጥጥር ስርዓት መፍጠር በማስፈለጉ ነው ጥናቱ የተካሄደው።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ሳይበር ደህንነት ጥቃት ሙከራዎች የቴክኖሎጂ ላይ ጥገኝነት በመጨመሩና ተደራሽነት በመስፋፋቱ ምክንያት እየጨመሩ መጥተዋል። ቁልፍ መሰረተ ልማቶችና አገልግሎቶች ላይ መስተጓጎል ሲፈጠር በሀገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ብሎም ሰላምና መረጋጋት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጠራል። ጥቃት ፈፃሚዎቹ ሀገራት፣ የሽብር ቡድኖች፣ ፅንፈኞች፣ የወንጀል ብድኖች ሊሆኑ ይችላሉ።

ቁልፍ መሰረተ ልማቶችን ከማስጠበቅ አንፃር እንደ ሀገር ከፖሊሲና ከሕግ አንጻር የተወሰዱ ርምጃዎች እንዳሉም አቶ ዳንኤል ይገልጻሉ በዳሰሳ ጥናቱም ክፍተቶችን መለየት ተችሏል ሲሉም ይገልጻሉ።

ከክፍተቶቹ መካካልም በሀገር አቀፍ ደረጃ ሕግን መሰረት ያደረጉ ቁልፍ መሰረተ ልማቶችን ለመለየት የሚያስችሉ መስፈርቶች አለመውጣታቸው፣ ብሔራዊ የሳይበር ደህንነት አመራር ቁልፍ መሰረተ ልማቶችን ቢለይም የሰነዱ አስገዳጅነት አናሳ መሆኑ እና መንግሥት ቅድሚያ በመስጠት ጥበቃ ሊያደርግላቸው የሚገቡ መሰረተ ልማቶችን በግልፅ አለመለየታቸው ይጠቀሳሉ።

ከፖሊሲና ስታንዳርድ አንፃርም እንዲሁ የተለዩ ክፍተቶች መኖራቸውን ገልጸው፣ ከፋይናንስ ተቋማት ውጪ የቁልፍ መሰረተ ልማት ተቋማት የራሳቸውን የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስታንዳርድ ማውጣትና መተግበር ላይ ክፍተት እንዳለባቸውም ያመለክታሉ። ፖሊሲ ያላቸው ተቋማት ቢሆኑም በየወቅቱ የመከለስና ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ላይ ክፍተቶች እንዳለባቸውም ተናግረዋል። ውስን ዘርፎች (የፋይናንስ ዘርፍ - በብሔራዊ ባንክ በኩል) የራሳቸውን ዘርፍ ተኮር የሳይበር ደህንነት ስርዓቶች በማውጣት ቢቆጣጠሩም፤ በአብዛኞቹ ዘርፎች ላይ ግን ክፍተቶች እንደሚስተዋሉ አመልክተዋል።

የመረጃ ልውውጥ ቁልፍ መሰረተ ልማት ተቋማት የሳይበር ስጋት፣ አደጋ ወይም ክስተት ሲያጋጥማቸው ሪፖርት የሚያደርጉበት አስገዳጅ ስርዓት አለመኖር፣ ተቋማት ከሀገራዊ የኮምፒውተር አደጋ ምላሽ መስጫ ማዕከል (ከኢትዮ-ሰርት) ጋር በቅንጅት መረጃ የሚለዋወጡበት ጠንካራና ሕግን መሠረት ያደረገ ስርዓት አለመኖሩ እና ክስተቶችን አስመልክቶ ከኢትዮ ሰርት የሚሰጡ መረጃዎችንና ማስተካከያዎችን ተቀብሎ ከመተግበር አንፃር ክፍተቶች እንዳሉም አቶ ዳንኤል አስታውቀዋል።

አቶ ዳንኤል እንዳብራሩት፤ ከቅንጅታዊ አሰራር ጋር ተያይዞም ክፍተቶች ይስተዋላሉ። ከእነዚህ መካካል ቁልፍ መሰረተ ልማቶችን የሚመሩ ዘርፎችን በማዕከል ደረጃ የሚያገለግሉ ዘርፍ ተኮር የኮምፒውተር አደጋ ምላሽ መስጫዎች (Sectorial CERT) የሉም። ከሳይበር ደህንነት ጋር የተያያዙ መረጃዎችን፣ እውቀቶችንና ልምዶችን ከተፈቀደላቸው አካላት ጋር መለዋወጥ የሚያስችለው አግባብ አነስተኛ ነው።

በብሔራዊ እና የተቋማት የሴክዩሪቲ ኦፕሬሽን ሴንተር አደጋ ምላሽ መስጫዎች ጋር ያለው ቅንጅትም እንዲሁ አነስተኛ መሆኑን ጠቅሰው፣ ከቁልፍ ተቋማት ጋር የሳይበር ደህንነት ስጋትን ለመቀነስ የሚደረግ የእውቀት ሽግግር ልምድ ልውውጥ ተግባራት አነስተኛ መሆናቸውም ገልጸዋል።

የሳይበር ደህንነትን ዋና ስራቸው አድርገው የሚሰሩ አደረጃጀቶችን ከመፍጠር አንፃር የተስተዋሉ ክፍተቶች እንዳሉ አቶ ዳንኤል ይጠቁማሉ። የደህንነት ኦፕሬሽን ማዕከሎችን (SOC) ከማደራጀት አንፃር በበርካታ ቁልፍ መሰረተ ልማት ተቋማት ዘንድ ውስንነት እንደሚታይም ነው ያመለከቱት። ዘርፍ ተኮር የኮምፒውተር አደጋ ምላሽ መስጫ ማዕከሎችን (Sectorial CERT) በማቋቋም ረገድም ክፍተቶች እንዳሉ ጠቅሰው፤ በዚህም የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የሀገራዊውን እንዲሁም የዘርፍ ክስተት አስተዳደሮችን እንዲሰራ መገደዱን አመላክተዋል።

ጥናቱ በአስገዳጅ ሕጎች ላይም ክፍተት እንዳለ ያመላክታል ያሉት አቶ ዳንኤል፤ ከብሔራዊ የኮምፒውተር አደጋ ምላሽ መስጫ ማዕከል የሚሰጡ ማስተካከያዎች አስገዳጅነት የሌላቸው መሆናቸውንም አንስተዋል። ከቁልፍ መሰረተ ልማቶች የሳይበር ደህንነት ጋር ተያይዘው የሚወጡ ስታንዳርዶችንና ስርዓቶችን ተግባራዊ በማድረግ በኩልም ክፍተት መፍጠሩን ገልጸዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የሳይበር ደህንነት ፍተሻና ግምገማ አስገዳጅነት የሌለው በመሆኑ ይህ ስራ ከዓለም አቀፍ ልምድ በተቃረነ መልኩ በተቋማት መልካም ፈቃድ ላይ መመስረቱ፤ በፍተሻና ግምገማ የሚሰጡ ማስተካከያዎችን ለማስተግባር አልተቻለም። በእነዚህም ምክንያቶች አስተዳደሩ በአዋጅ በተጣለበት ኃላፊነት መሰረት ክትትልና ድጋፍ የማድረግ፣ መረጃ የመለዋወጥ እንዲሁም ሌሎች የቁጥጥር ስራዎችን በመስራት በኩል እክሎች እየተፈጠሩበት ናቸው። በቸልተኝነት ጉዳት እንዲደርስ የሚያደርጉ አካላትን ተጠያቂ ማድረግም አልተቻለም።

በአስተዳደሩ በኩል የሳይበር ደህንነትን ከማስጠበቅ አንጻር በርካታ ሥራዎች መሰራታቸውንና የተወሰዱ እርምጃዎች እንዳሉም አመልክተው፣ ከፖሊሲ አንጻር ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ እንዲፀድቅ ተደርጓል ይላሉ። በፖሊሲውም የቁልፍ መሰረተ ልማት ጥበቃ አንድ የትኩረት አቅጣጫ እንዲሆን ሁሉን አቀፍ የቁልፍ መሰረተ ልማቶች ደህንነት ረቂቅ አዋጅ በማዘጋጀትና ረቂቅ የሕግ ማዕቀፉን በሁለት ሀገራዊ መድረኮች በመፍጠር እና በፍትሕ ሚኒስቴር ማስተቸት የቁልፍ መሰረተ ልማቶችን የቴክኖሎጂ የአቅርቦት ሰንሰለትን ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የቴክኖሎጂ ቁጥጥር አዋጅ ማፀደቅ ተችሏል።

በሬጉላቶሪ በቁልፍ መሠረተ ልማት ዘርፍ ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች የሀገራዊ ሕጎችን መነሻ በማድረግ ዘርፉን ልዩ ባሕሪ ታሳቢ ያደረጉ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና አስገዳጅ ማሕቀፎችን ማልማት ያስፈልጋል ሲሉም ጠቁመዋል። የዘርፉን የሳይበር ደህንነት ክስተቶች ሪፖርት የሚቀበልና ምላሽ የሚሰጥ አደረጃጀት መፍጠር ይጠበቃል ሲሉም ገልጸዋል።

ለዚህም የአመራር ቁርጠኝነት እንደሚያስፈልግ፣ በቂ ፋይናንስ በመመደብና ዘርፉን በቴክኖሎጂና በሰው ኃይል አቅም መግራት እንደሚገባም አስታውቀዋል። የዘርፉን ክፍተቶች በመለየት ለፋይናንስ ተቋማት ብሎም ለራሱ አባላት አቅም ግንባታና ግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም መተግበር እና የዘርፉ ተዋናዮች ስራ ላይ የሚገኙ የደህንነት ማዕቀፎችን መሰረት አድርገው መስራታቸውን መቆጣጠርና እርምጃ መውሰድ ወይም ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ሲሉ አስገንዝበዋል።

ጥናቱ በመፍትሔነት ካስቀመጣቸው መካከልም በቁልፍ መሰረተ ልማት ተቋማት በሳይበር ደህንነት ፕሮግራም፣ በሰው ኃይል አቅም ግንባታ፣ በአደረጃጀትና በቂ ሀብት በመመደብ ላይ ሊወሰዱ የሚገባቸው የመፍትሔ እርምጃዎች እንዳሉም አቶ ዳንኤል ጠቁመው፣ ከሳይበር ደህንነት አንጻር አደጋ ትንተና ላይ የተመሰረተ ስትራቴጂክ፣ ታክቲካልና ኦፕሬሽናል እርምጃዎችን መውሰድ እንደሚስፈልግ ይገልጻሉ።

የሰው ኃይል አቅም ግንባታ ስራው የምስክር ወረቅት /ሰርቲፋይድ የሆኑ/ እና ደህንነት ማረጋገጫ ያላቸው ባለሙያዎች መቅጠርን፣ ቀጣይነት ያለው የአቅም ግንባታና ግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠትን እንደሚጠይቅ አንስተዋል። ከአደረጃጀት ጋር ተያይዞም እንዲሁ እንደሚያስተዳድሩት ሃብት ተመጣጣኝ የሳይበር ደህንነት እና ክስተት አስተዳደር መፍጠር እንደሚገባ ጠቅሰው፤ በቂ ፋይናንስ ወይም ሀብት በመመደብ አቅምን ማጠናከር እንደሚያስፈልግ አስገንዝበዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ የሳይበር ጥቃት ከቴክኖሎጂው እድገት ጋር እየተወሳሰበ እና እየተራቀቀ መምጣቱን ጠቅሰው፣ እያደረሰ የሚገኘውም ጉዳት እጅግ ከፍተኛ መሆኑን አቶ ዳንኤል፤ የሳይበር ደህንነት ጉዳይ የተቋማት ብቻ እንዳልሆነም አስታውቀው፣ የብሔራዊ ደህንነት የሀገር ሉዐላዊነት ጉዳይ መሆኑን ገልጸዋል። የሳይበር ምህዳር ተግዳሮቶችን ለመፍታት ሁሉም በጋራ ሊረባረብ እንደሚያስፈልግ አመላክተዋል።

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የባሕር በርን በተመለከተ የሚካሄድ ትግል

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

ኢትዮጵያ በአፍሪካ የባሕር በር ከሌላቸው አስራ ሰባት ሀገሮች ሕዝቦች የሲሶው መኖሪያ ናት። አንድ መቶ ሀያ ሚሊየን የሚጠጋ ሕዝብ ይዞ የባሕር በር የሌለው ሀገርም ከኢትዮጵያ ውጪ ማንም የለም። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በሕዳር ወር 2016 ዓ.ም የቀይ ባሕር አስፈላጊነትንና የባሕር በር ጉዳይን በተመለከተ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማብራሪያ ካቀረቡበት ጊዜ አንስቶ በጉዳዩ ዙሪያ የተለያዩ ሃሳቦች ሲሰነዘሩ ቆይተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የቀይ ባሕር የጋራ ተጠቃሚነትም ሆነ የባሕር በር ጥያቄ መጠየቅ ለኢትዮጵያ ትርፍ ጥያቄ ሳይሆን የሕልውና ጉዳይ እንደሆነም አስረድተዋል። የኢትዮጵያ ሕልውና እና ልዕልና ከቀይ ባሕር ጋር የተሳሰረ ነው። የኢትዮጵያ የዘመኑ ስትራቴጂካዊ ዕቅድ ሠላምና አንድነትን ማስፈን፣ ሁለንተናዊ ብልጽግና ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያ በውሃ ተከባ ነገር ግን ውሃ የሚጠማት ሀገር ናት፣ ቀይ ባሕርና ዓባይ ኢትዮጵያን የሚበይኑ ከኢትዮጵያ የተቆራኙ ለኢትዮጵያ እድገትና ጥፋት መሠረት ናቸው። የኢትዮጵያ የባሕር በር ባለቤት የመሆን ታሪክ ብቻ ሳይሆን ኢኮኖሚ ጭምር ነው፤ ሰላማዊ በሆነ መንገድ የባሕር በር ፍላጎቷን ማሳካት ትፈልጋለች ብለዋል።

አሁን አይቻልም ማለት ነገ አይቻልም ማለት ባለመሆኑ ተነጋግሮ ከተሳካ ይሳካል እንጂ ተዳፍኖ ይቅር የሚባል አይደለም ብለውም ነበር። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በቀጥታ በጉዳዩ ላይ ቅሬታ ካሰማችው ሱማልያ ጋር አንዳንድ ሀገራትም በጉዳዩ ዙሪያ እያንዣበቡ ይገኛል። ለመሆኑ ኢትዮጵያ እየሰራችበት ባለው የባሕር በር የማግኘት እንቅስቃሴ የአንዳንድ ጎረቤት ሀገራት ምላሽ ለምን ቀና አልሆነም ስንል ባለሙያዎችን አነጋግረናል።

በዲፕሎማሲ እና ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ተመራማሪና የሰላምና የጸጥታ ጉዳዮች አማካሪ አቶ ደሳለኝ ማስሬ ላነሳንላቸው ጥያቄ በሰጡን ምላሽ ላይ እንዳብራሩት፤ ኢትዮጵያ በራሷ የምትቆጣጠረው በራሷ የምታለማው የባሕር በር እንዲኖራት የተለያዩ ተግባራትን ስታከናውን ቆይታለች።

ነገር ግን በቅርቡ ከሱማሌ ላንድ ጋር ያደረገችው የመግባቢያ ስምምነት ተከትሎ የተለያዩ ሀገራት እያደረጉት ያለውን እንቅስቃሴ አይተናል። የእዚህም መነሻ ሊሆን የሚችለው አንደኛው ኢትዮጵያ የባሕር በር ካገኘች በቀጣናው ያላት ተቀባይነት እየጨመረ መምጣቱ አይቀርም። ይህም ለሀገሪቱ በፖለቲካና ኢኮኖሚው መስክ ተቀባይነት ከማስገኘት ባለፈ በጸጥታው ዘርፍ ከፍተኛ አቅም ስለሚፈጥር የበላይነታችንን እናጣለን ከሚል ስጋት ነው።

ሌላኛው ምክንያት የኢኮኖሚ ጉዳይ ነው። እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ዘጠና በመቶ የሚሆነውን የወጪ ንግድ የምታስተናግደው በጎረቤት ሀገራት በኩል ነው። ጅቡቲ ከዓመታዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዋ ስልሳ በመቶ የሚሸፈነው ኢትዮጵያ በጅቡቲ ወደብ በምታስገባቸውና በምታስወጣቸው ምርቶች ነው። ይህንን መሰረት በማድረግ ኢትዮጵያ የራሷ የባሕር በር ካላት፤ ይህ ነገር ሊቀንስ ይችላል ወይም ሙሉ ለሙሉ ይቋረጣል የሚል ስጋት አለ።

ኢትዮጵያ ለኢኮኖሚያዊ እድገቷ ፈታኝ ከሆኑባት ጉዳዮች ቀዳሚው የራሷ የባሕር በር አለመኖሯ ነው። በዚህም በአገሪቱ በዓመት ከሁለት ቢሊየን ዶላር በላይ ለባሕር በር አገልግሎት ትከፍላለች። የባሕር በር ባለቤት ከሆነች፤ ይህ ገንዘብ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መስክ በሀገር ውስጥ ሊያስገኝ የሚችለውን ጠቀሜታ ማሰብ ቀላል ነው ይላሉ።

በሌላ በኩል የጸጥታ ጉዳዩም ከግምት ይገባል። ቀኝ ገዢ የነበሩት አውሮፓ ሀገራት ወደ ቀጣናው ይገቡ የነበረው በቀይ ባሕር በኩል ነበር። ኢትዮጵያ የራሷን የባሕር በር በምታስተዳድርበት በዛ ዘመን እነዚህን ቀኝ ገዢዎችና ከጎረቤት ሀገራት የሚመጡ ወራሪዎች አሳፍራ ለመመለስ ችላለች።

ከዛ በኋላም ኢትዮጵያ የኤርትራ መገንጠልን ተከትሎ የባሕር በር አልባ ከሆነች በኋላም ለራሷ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ሀገራትም በሰላም ማስከበር ተልዕኮ ጠንካራ አቅም ያላት ሀገር መሆኗን አስመስክራለች። በዚህ መነሻነት ሀገሪቱ የባሕር በር ካገኘችና የራሷን የባሕር ኃይል መገንባት ከቻለች በአካባቢው ጠንካራ ኃይል ትፈጥራለች የሚልም ስጋትም ያለባቸው መሆኑን ይገልፃሉ።

እንደ አቶ ደሳለኝ ገለፃ፤ እነዚህ ነገሮች ጠቅለል ተደርገው ሲታዩ በአንድ ወገን እንደ ጅቡቲ ያሉ ሀገራት የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸውን መነሻ በማድረግ ጥቅም እንዳይቋረጥባቸው ሲሉ የሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች አሉ። በሌላ በኩል እንደ ኤርትራ ያሉ ሀገራት ኢትዮጵያ እየተጠናከረች መምጣት ካላቸው ታሪካዊ ግንኙነት አኳያ ስጋት ትሆንብናለች በሚል ነው።

ዋናዋ ተቃዋሚ ሶማልያ ባለፉት ሰላሳ ዓመታት ይህ ነው የሚባል መንግስት ያልመሰረተች የራሷን ሰላምና ደህንነት በቅጡ ማስጠበቅ ያልቻለች ሀገር ናት። አልሸባብና ሌሎች የታጠቁ ኃይሎች ዛሬም ድረስ እንዳሻቸው እያመሷት ይገኛል። በየአካባቢው ካለው አስተዳደር ይልቅ በየመንደሩ ያሉ ታጣቂዎች ተሰሚነትና ተቀባይነት የሚያገኙባት ሀገር ናት።

አሁን ያሉት ፕሬዚዳንትም በቅርብ የመጡ ቢሆንም በሕዝብ ዘንድ ያላቸው ተቀባይነት እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። በመሆኑም ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም የሀገራችንን ዳር ድንበር አስከብራለሁ በሚል ሰበብ ተቀባይነትና ተደማጭነት ለማግኘት የመረጡት አካሄድ ነው። ይህን የሚያሳየው ሶማልያ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ሕብረት ስብሰባ ተጽእኖ አሳድራብኛለች የሚል ወሬ በመንዛት እና ስም በማጥፋት የአፍሪካ ሕብረት ከአዲስ አበባ እንዲነሳ ሞክራለች።





**ከኢትዮጵያ ጋር ስምምነት ያደረገችው ሱማሌ ላንድ እንደ ሀገር ቆማ ራሷን ማስተዳደር ከጀመረች ከሰላሳ ዓመት በላይ ሆኗታል**

ከግብጽና ከሱዳን ጋር በመሆን ኢትዮጵያን ጸብ አጫሪ ሀገር ተብላ እንድትፈረጅም ሲሰሩ ነበር። ሌላው ከሕዳሴው ግድብና ከሌሎች ታሪካዊ ግንኙነቶች በመነሳት ግብጽ ኢትዮጵያን ደካማና ሁል ጊዜ በፈተናዎች የታጀበች ሀገር ለማድረግ የጀመሩት እንቅስቃሴ ነው።

ይህም ሆኖ ጥያቄው ተገቢና ፍትሃዊነት ያለው በመሆኑ በኢትዮጵያ በኩል እንደቀጠለ ይገኛል። በመሰረቱ ኢትዮጵያ በታሪኳ የትኛውንም ሀገር ወርራ አታውቅም። የትኛውንም ሀገር ጥቅም ለማሳጣትም ተንቀሳቅሳ አታውቅም። አሁንም እየተንቀሳቀሰች ያለችው የየትኛውንም ሀገር ሉአላዊነት እና ጥቅም በሚጋፋ መልኩ አለመሆኑ ጥያቄው የጊዜ ጉዳይ እንጂ መሳካቱ አንደማይቀር አመላካች ነው ይላሉ።

በተመሳሳይ «ኢትዮጵያ የባሕር በር የምትፈልገው በሌሎች ላይ ለመዝመት ወይም ተጽእኖ ለማሳደር አይደለም።» የሚሉት ደግሞ የታሪክ ተመራማሪ ፕሮፌሰር አደም ካሚል ናቸው። ፕሮፌሰር አደም እንደሚገልጹት፤ ኢትዮጵያ የባሕር በር የሚያስፈልጋት ምርቶቿን ወደ ውጪ በመላክና ገቢ በማግኘት ስራ አጥነትን ለመቅረፍ ብሎም ሕገወጥ ፍልሰትን ለማስቀረት እና አጠቃላይ ድህነትንን ለማጥፋት ነው።

ኢትዮጵያ ከውጪ የምታስገባው ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ምርት ወደ ውጪ የምትልከውም ስላላት ደህንነቱ የተጠበቀ የንግድ ልውውጥ እንዲኖር ወደብ የማስፈለጉ ጉዳይ አጠያያቂ አይደለም። በኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ የሶማልያም ሆነ የሌሎች ሀገራት ቅሬታ ውስጥ መግባትም ጥቅማቸውን መሰረት በማድረግና ኢትዮጵያን ለማዳከም በማሰብ እንጂ ውሃ የሚቋጥር ስጋት ስላለባቸው አይደለም። ለምሳሌ በአሁኑ ወቅት ግብጽ ውስጥ ሰላሳ ሺህ የሚሆኑ የሳውዲ ኩባንያዎች ሰባት ቢሊየን ዶላር የሚደርስ ካፒታል በመያዝ እየተንቀሳቀሱ ናቸው።

የገልፍ ሀገራት ደግሞ የምግብ ዋስትና እና የውሃ ችግር አለባቸው። ግብጾች እነዚህን ሁሉ የሚያስተናግዱትና ለዚህ ምላሽ የሚሰጡት ከኢትዮጵያ በአባይ አማካይነት የሚሄደውን ውሃና ለም አፈር በመጠቀም ነው። በመሆኑም ኢትዮጵያ ሰላም ካገኘችና አንድነቷን ማጠናከር ከቻለች እነዚህን ኢንቨስተሮች ይነጥቁናል የሚልም ስጋት አለባቸው። በእርግጥም ኢትዮጵያ ሰላም ከሆነች ምርቶቿን ከመላክ ለኢንቨስትመንት ምቹ ከመሆን ባለፈ በቱሪዝምም ተመራጭ ሀገር መሆኗ አይቀርም ይላሉ።

ከረሀብ እንውጣ፤ ከድህነት እንውጣ፤ ከኋላ ቀርነት እንውጣ የሚል ለውጥ እየታወጀ ባለበት በአሁኑ ወቅት ግብጾች ኢትዮጵያ ከበለጸገች ለእኛም ሆነ ለአካባቢው ስጋት ትሆናለች ብለው ያስባሉ። በመሆኑም ይህንን ለመቀልበስ ማዳከም አለብን በማለት አጀንዳ አስቀምጠው ውስጥ ለውስጥ እየሰሩበት ይገኛል። ይህ ነገር በተለይ የግብጾችን ሚድያ ለሚከታተል ሰው አዲስ አይሆንም። ግብጾች በርካታ ሚድያዎች ያላቸው ሲሆን፤ ለቁጥር የሚታክቱ ጋዜጠኞችን በዚህ ላይ እያሰሩ ይገኛሉ። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ኢትዮጵያ አሁንም በዲፕሎማሲው መስክ ጥሩ እንቅስቃሴ ማድረግ ከቻለች ለኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ በአረቡ ዓለም ዘንድ የተለየ ቦታ የሚኖራት ይሆናል ብለዋል።

በሌላ በኩል ጸጥታን በተመለከተ ቀይ ባሕር ራሱ አካባቢው ሰላም አለመሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነው። መካከለኛው ምስራቅ እስራኤል፤ ኢራን፤ የመን አጠቃላይ አካባቢው ቀውስና ጦርነት ውስጥ ናቸው። በዚህ ሂደት ደግሞ ሁሉም የቀጣናው ሀገራት ሲመቻች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በጉዳዩ ውስጥ እጃቸውን ሲያስገቡ ይታያል።

እዚህ ላይ ዋናው መታየት ያለበት፤ ነገር ለምን የባሕር በር ጥያቄና ከሌሎች ሀገራት ጋር የሚደረግ የግንኙነት ጉዳይ የኢትዮጵያ ሲሆን፤ በልዩነት ይታያል የሚለው ነው። ከዚህ ቀደም አረብ ኢምሬትስ በበርበራ ላይ ስምምነት አድርገው ፊርማ ተፈራርመዋል።

የዛን ጊዜ እንኳን የዚህ ያህል ጩኸት ይቅርና ምንም የተባለ ነገር አልነበረም። ዛሬ ከኢትዮጵያ ጋር ስምምነት ያደረገችው ሱማሌ ላንድ እንደ ሀገር ቆማ ራሷን ማስተዳደር ከጀመረች ከሰላሳ ዓመት በላይ ሆኗታል። ከተለያዩ ሀገራትም የውስጥ እውቅናን አግኝታለች ይህ ሁሉ ሲሆን፤ ምንም ሳይባል ኢትዮጵያ ላይ ብቻ ወንጀል እና ነውር ተደርጎ ሊወሰድ የሚችልበት ሁኔታ መኖር የለበትም።

ይህም ሆኖ የተጀመረውን ከግብ በማድረስ የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ ለግብጻውያን በቀጥታ ከሕዳሴው ግድብ ጋር የሚያያዝ በመሆኑ በግብጽ በኩል እየተሰሩ ያሉ ሴራዎችን ለማክሸፍ በርካታ ስራዎች ይጠበቃሉ። ለምሳሌ ከሀይማኖት ተቋማት ጀምሮ የየትኛውም ሀይማኖት መሪ በበቂ ሁኔታ እየሠራ አይደለም ለማለት እችላለሁ። ከግብጽ እንቅስቃሴ አኳያ እዚህ ግባ የሚባል ትልልቅ ሥራ እየተሠራ አይደለም።

በተለይ በሚድያ ዘመቻ ረገድ ምንም እየተሰራ አይደለም ለማለት ያስደፍራል። የሀገር ውስጥ ሚድያዎች በሙሉ የግልም የመንግስትም ትኩረታቸው ሁሉ በሌሎች ጉዳዮች ላይ ነው። በአንጻሩ ግብጾች የራሳቸውን ብቻ ሳይሆን የአረቡን ዓለም ሚድያ ሁሉ ተቆጣጥረው እኩይ ዓላማቸውን ለማሳካት እየተጠቀሙበት ይገኛል። በኢትዮጵያ በኩል ይኸው ሊደረግ ይገባል። ይህ የሀገር የትውልድ ጉዳይ ነው ይላሉ።

በውጨው ዓለም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንም የሚጠበቅባቸው በርካታ ስራ አለ። አስር ሚሊየን የሚደርሱ ግብጻውያን ከሀገራቸው ውጪ በስደት እንደሚኖሩ ይገመታል። ስምንት መቶ ሺ የሚደርሱ በተለያዩ ሀገራት የሚገኙ ኤክስፐርቶች አሏቸው። እነሱ በሁሉ በየሚዲያው በተለይ በአረብኛ በሚተላለፉት ላይ በዚህ ጉዳይ በንቃት ይሳተፋሉ። የባሕር በር የማግኘት ጉዳይ የአንድ አካባቢ ጥያቄ ሳይሆን የመላው ኢትዮጵያዊ ነው። ዲፕሎማቶችም አረብኛ ቋንቋ የሚችሉ የአካባቢውን ባህሉን የሚያውቁ መመደብ አለባቸው። በመንግስት በኩልም ለብዙሀኑ ተደራሽ እንዲሆን የፓናል ውይይቶችን ከማድረግ ጀምሮ በርካታ ስራዎች የሚጠበቁ ይሆናል።

የቀድሞ የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ ከዚህ ቀደም የሕዳሴን ግድብ በተመለከተ የተናገሩትን እናስታውሳለን። አሁን ደግሞ በምርጫ እየተወዳደሩ ነው ቢያሸንፉ አጠቃላይ በኢትዮጵያና በግብጽ ግንኙነት ላይ የሚኖራቸው አቋም ምን ይሆናል የሚለውም መታየት አለበት። ለዚህ ደግሞ በአሜሪካ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ብዙ ይጠበቃል።

በእርግጥ በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እስካሁን ድረስ ትኩረት ያደረጉት በሌሎች ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ መሆኑ ግልጽ ነው። ነገር ግን በዚህ ጉዳይ ያኮረፉ አካላትም ቢሆኑ የተለየ ትኩረት ሊሰጡት የሚገባ ነገር መሆኑን ሊገነዘቡ ይገባል። ያም ሆነ ይህ የውስጥ ሰላም ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ከተቻለ የባሕር በር ጥያቄው ዛሬም ባይሆን ነገ ምላሽ ማግኘቱ አይቀሬ ነው።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# የሶፍት ዌር ምሕንድስና ተማሪዋ ጂቱ እውነቱ

**አመስወርቅ ከበደ**



የዛሬዋ እንግዳችን ጂቱ እውነቱ ትባላለች:: ያገኘናት በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ14ኛ ጊዜ፤ በኢትዮጵያ ደግሞ ለ12ኛ ጊዜ ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ባዘጋጀው "ታዳጊ ሴቶች ላይ መስራት የነገን የተሻለች ሀገር መገንባት ነው "በሚል መሪ ቃል ዓለም አቀፍ የታዳጊ ሴቶች ቀን፤ የታዳጊነት እና የዩኒቨርሲቲ ተሞክሮዋን ለታዳጊዎች ለማካፈል በመጣችበት ወቅት ነው::

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአምስተኛ ዓመት የሶፍት ዌር ምህንድስና ተማሪ ናት:: በታዳጊነት እድሜዋ የወደፊት ህልሟን አስረግጣ ስትናገር ሴት በመሆኗ ልታሳካው አትችልም በሚል እሳቤ በአካባቢዋ ያሉ ሰዎች ይዘብቱባታል:: ይህን የማህበረሰቡን ጫና ተቋቁማ ከፍተኛ ውጤት አምጥታ ዩኒቨርሲቲ ስትገባ ያልጠበቀችው ፈተና ገጥሟታል:: ይህን መነሻ በማድረግ የማህበረሰብ ተጽኖ ተቋቁመው እንዴት ማለፍ እንደሚችሉ ምክሯን ትለግሳለች::

ውልደቷ በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን መንዲዳ በምትባል ትንሽዬ ከተማ ነው:: ቤተሰቦቿ በስራ ምክንያት ወደ ጅማ ከተማ በመሄዳቸው፤ የሁለት ዓመት ልጅ እያለች ወደ ጅማ ከተማ መጥታ አደገች:: የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ያጠናቀቀችው እዛው ጅማ ከተማ ነው::

ጂቱ በትምህርቷ ቀለመቀንድ የምትባል አይነት ተማሪ ናት:: የወላጆቿም ድጋፍ ተጨምሮ የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ስትከታተል ሁሉንም የክፍል ደረጃዎች ተሸላሚ ሆና አጠናቅቃለች:: የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ውጤቷም ከትምህርት ቤቱ ሁለተኛው ከፍተኛ ውጤት ነበር::

ለሳይንስ ትምህርት ከፍተኛ ፍቅር እንደነበራት የምትገልጸው ጂቱ፤ "አሁን ለምማረው የትምህር ዘርፍ እና ለቴክኖሎጂ ያለኝ ፍቅር እየጨመረ የመጣው ከፍ እያልኩ ስመጣ ነው:: በፊት ‹አስትሮኖሚ› የሚባሉ ቃላቶችን ስለምሰማ ስለቴክኖሎጂ ለማወቅ ጉጉት ነበረኝ::" ስትል ትናገራለች::

ዝንባሌዋ ወደ ቴክኖሎጂ እንዲሆን የቻለበትን አጋጣሚ ስታስታውስ፤ እንዲህ ትላለች፤ "በአጋጣሚ አባቴ ‹አይ ቢ ኤም› የሚባል ኮምፒውተር ነበረው፤ የኮምፒተር እውቀት ባይኖረኝም ዝምብዬ እነካካው ነበር:: እያደኩ ስመጣ ቴሌቪዥን እና ስልክ ማየት ጀመርኩ::" ትላለች::

"በተመሳሳይ ሁኔታ ደግሞ ሴት ስትሆኚ ማህበረሰቡ ይገድባል:: ፍላጎትሽን ለመምረጥ ይሞክራል፤ አትችይም፤ ይሄ ላንቺ አይሆንም የሚሉ ድምጾች ሲበዙ ወደዚህ ዘርፍ ለመግባት ይበልጥ ጓጓሁ:: ይቅርብሽ የሚሉ ሀሳቦች ሲበዙ፤ ይሄ ነገር ምን ቢሆን ነው? በሚል ይበልጥ እልህ ውስጥ ልገባ ቻልኩ::" ስትል ታስረዳለች::

አንድ ሰው በማህበረሰብ ውስጥ እስከ ኖረ አብሮ መብላቱ፣ አብሮ ማውራቱ አይቀርም:: ጂቱ ከሰዎች ጋር ቀርባ ስታወራ ምን መሆን እንደምትፈልግ ሲጠይቋት፤ ፍላጎቷ መሀንዲስ መሆን እንደሆነ በልበ ሙሉነት እና በየዋህነት ስትናገር፤ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የራሳቸውን ፍላጎት ለእሷ እንደሚሆን በማሰብ ይሄኛው አይሻልሽም ሲሏት ትበሳጭ እንደነበር ትናገራለች::

ሌላው ከዚህ በፊት በዚህ ዘርፍ ስኬት ላይ የደረሰ አራያ የሚሆን ሴት አለመኖሩን በመግለጽ፤ ከዚህ በፊት ያሳኩት ስለሌሉ እሷም እንደማይሳካላት ተስፋ አስቆራጭ አንደበታቸውን አዛኝ መስለው ይናገሯት እንደነበርም ታስታውሳለች:: እሱ ብቻ ሳይሆን "ትምህርቱ ረጅም ዓመት የሚወስድ ስለሆነ ሴት ስለሆንሽ እድሜሽ ይሄዳል:: ከዛ ስትወጪ ማን ያገባሻል" የሚሉ ስሜቷን የሚነኩ ንግግሮች እንደነበሩም ትናገራለች::

"ጥሩ ነገር አይደለም እያልኩ ባይሆንም፤ ሴት ስትሆኚ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚጠበቀው ቶሎ ወጥተሽ እንድታገቢ እና እንደወትወልጂ ነው:: ሁሉም ሰው በሚፈልገው ጉዳይ ሴቶችን ሊመራ ይፈልጋል:: "በማለት ትገልጻለች::

ዩኒቨርሲቲ እስከምትገባ ሶፍት ዌር መሀንዲስ ለመሆን ውስን እና የተደራጀ ህልም አልነበራትም:: ነገር ግን ህልምና ዝንባሌ ነበራት:: ህልሟ መሀንዲስ መሆን ሲሆን፤ ዝንባሌዋ ለኮምፒውተር ያላት ፍቅር ነው:: ሁለተኛ ደረጃ ስትደርስ ባደገችበት ከተማ እንደ አዲስ አበባ ብዙ ቴክኖሎጂን የተመለከቱ ዝግቶች እና ስልጠናዎች ባለመኖራቸው ወደ ዩኒቨርሲቲ ጊቢ የገባቸው መሰረታዊ የኮምፒውተር እውቀቶችን ብቻ ይዛ ነበር::

"ወደ ምህንድስና ትምህርት መጀመሪያ ሲገባ የሚሰጥ "ኮርስ" አለ:: የዛኔ ነው ስለ ሶፍት ዌር በደንብ ማወቅ የቻልኩት:: ከተነሳ አይቀር ሌላው የተሳሳተ ግንዛቤ ደግሞ "ኮዲን" ቀድመሽ የማታውቂ ከሆነ ሶፍት ዌር መሀንዲስና ይከብድሻል፤ የሚገቡት ቀድመው ብዙ ያወቁ ሰዎች ናቸው የሚሉም አልታጡም::" ትላለች

"እውነታው ግን እንደዛ አይደለም፤ ወደ ትምህርት ዘርፉ ከተገባ በኋላ ሁሉንም ነገር ከአንድ ጀምሮ መማር ይቻላል:: እኔ ከሶፍት ዌር እና "ኮዲንግ" ጋር ተያይዞ እያንዳንዱን ነገር ያወኩት ወደ ትምህርቱ ከገባሁ በኋላ ነው:: የግድ ቀድሞ "ጂኒስ " መሆን አይጠበቅም:: "ስትል ታብራራለች::

"ይህ ነገር የብዙ ሴቶችን ተነሳሽነት ሲገድል ስለምመለከት ነው:: አንድ ሰው ፍላጎቱ ካለው እና መማር እንደሚፈልግ ካወቀ በስድስት ወራት ውስጥ ሊረዳው የሚችለው ነው:: " ትላለች::

ቴክኖሎጂ እንደየግለሰቡ አጠቃቀም ገዳይም፣ ትንሳኤም ነው:: ጂቱ የቴክኖሎጂን አቅም ለትንሳኤ አድርጋዋለች:: ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ስትማር የጥናት ፕሮግራሟ አሰልቺ እንዳይሆን እና ከመምህሮቿ ከምታገኘው እውቀት ውጭ የተለያዩ እውቀቶችን ፍለጋ እንድትሰበስብ የቴክኖሎጂ ሚና ከፍተኛ ነው::

"12ኛ ክፍል ስማር የንባብ ፕሮግራሜን የማስኬድበት የራሴ መንገድ አለኝ:: በአንድ ጊዜ ብዙ አላነብም:: የማስኬደው ቀስ እያልኩ ነው፤ መጻፍ ሳነብ ከሰለቸኝ፤ ዩቱብ ላይ የሚለቀቁ የፊዚክስ፣ ኬሚስትሪ እና የሂሳብ ትምህርቶችን ለረጅም ሰዓት እከታተላለሁ:: ከዛን ቀድሞ የተሰሩ የፈተና ጥያቄዎችን እሰራለው::" ስትል ትናገራለች::

"እንዳይሰለቸኝ የማነበው እየቀያየርኩ ነው:: ምክንያቱም ማጥናት፤ አጥኚ እንደሚባለው ቀላል አይደለም:: እኔ 12 ክፍል በነበርኩበት ጊዜ ደግሞ በኮረና ምክንያት ትምህርት ተቋርጦ፤ ሞዴል ፈተናም አልወሰድንም ነበር:: ያመጣውት የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ውጤቴ 570 ነው:: በወቅቱ በትምህርት ቤታችን ሁለተኛው ከፍተኛ ውጤት ነው::" ትላለች::

ጂቱ ውጤት አምጥታ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከተመደበች በኋላ፤ ሴት በመሆኗ ከአካባቢው እርቃ መሄዷ ጥሩ ስለማይሆን እዛው ጅማ ዩኒቨርሲቲ ገብታ ብትማር መልካም እንደሚሆን አንዳንድ ሰዎች እናቷን ሲመክሯት ተደብቃ ትሰማ እንደነበር በማንሳት፤ ማህበረሰቡ ሴት ልጅ መሀንዲስ እሆናለሁ ከአካባቢዬ ርቄ መሄድ እችላለሁ ስትል «አትችይም» ይላል:: ነገር ግን ወንድ ልጅ በሰማይ ላይ እራመዳለሁ ቢል የሚሰጠው ምላሽ አወንታዊ ነው:: ስትል ገልጻለች::

"ታዳጊ ሴቶች ሰው ህልማቸውን እንዲቀይር መፍቀድ የለባቸውም" የምትለው ተማሪ፤ አንድ ሰው ወደም ይሁን ሳይወድ እሱ ይጠቅማል የሚለውን ነገር ለመናገር ይሞክራል:: ግን እንደዛ መሆን የለበትም ታዳጊ ሴቶች ማድረግ እንደሚችሉ እንዲያምኑ መፍቀድ ያስፈልጋል ትላለች

አንድ ተማሪ ተሳክቶለት ዩኒቨርሲቲ ሲገባ መጀመሪያ ከቤተሰቦቹ እና ካደገበት አካባቢ ተለይቶ የሚወጣበት እና አዲስ ጓደኛ አዲስ የኑሮ ዘይቤ የሚማርበት ነው:: ተብሎ ይታመናል:: ከነገሮች አዲስ መሆን ያለፈ ከቤተሰብ መራቅን ተከትሎ የተለያዩ ፈተናዎች የሚያጋጥሙበት ጊዜ ነው:: ይህ በወንድም በሴትም ላይ ያለ ነው:: ነገር ግን ይህ ፈተና ደግሞ ሴቶች ላይ ጠንከር የሚል መሆኑን መካድ አይቻልም::

አንዳንዶች ያጋጠማቸውን ተግዳሮት አሸንፈው እራሳቸውን በመገንባት ወደ አዲስ አስተሳሰብ እና የሕይወት ምዕራፍ ሲሻገሩ፤ ሌሎች ደግሞ ከቤታቸው ሲወጡ የነበራቸው ሰብእናም ጭምር ተጎድቶ ችግር ውስጥ እንደሚገቡ ነጋሪ የማያስፈልገው እውነት ነው::

ጂቱ ወደ ዩኒቨርሲቲ ስትገባ ያጋጠማት ፈተና ከጠበቀችው በላይ እና ከተለመደው የተለየ እንደነበር በመግለጽ፤ "ከታች ክፍሎች አንድ ችግር ካጋጠመ እሮጠን ቤታችን እንገባለን፣ እናታችን ጋር ገብተን ማልቀስ እንችላለን:: እቤት እያለው የማውቀው ጓደኞቼን እና ቤተሰቦቼን ነው:: ጊቢ ግን የምንኖረው ከተለያዩ አካባቢ ከመጡ ሰዎች ጋር ነው:: " ትላለች::

"እናም ሳልወድ በግዴ የሰዎችን ባህሪ መልመድ አለብኝ:: እቤት ውስጥ እህት ወንድሞቼ እኔ በመሆኔ የሚችሉት ባህሪ ይኖራል:: ነገር ግን ዩኒቨርሲቲ ስገባ እንደዛ አይደለም፤ እንደፈለጉ መሆን አልችልም፡ መተው ያለብኝ ባህሪ ይኖራል:: ለኔ የሰዎችን ባህሪ መልመድ ትንሽ ከብዶኝ ነበር:: በአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲ ሕይወትን ተምረን የምንወጣበት ተቋም ነው::" ስትል ታስረዳለች::

"አብዛኛው ሰው የሴት ልጅ ጥቃት ሲባል የሚያውቀው መደፈርን ብቻ ነው:: እንዲ ካላደረግሽ እንዲህ አደርግሻለው የሚል ዛቻ፤ መንገድ ላይ የሚላከፍ ሰው እና በጣም ብዙ ጥቃት አለ:: ለዚህ ደግሞ መክሰስ አይቻልም::" ትላለች ::

"እንደዚህ አይነት ነገር ቀላል አይደለም፤ በጣም ከባድ ነው:: የስነልቦና ጫናው ትምህርትም ላይ የሚፈጥረው ተፅኖ ከፍተኛ ነው:: ለምሳሌ አንድ ሰው ሴት ስለሆንኩ ተናግሮኝ ፊት ነስቼው፤ ቀጣይ ቀን ዝቶብኝ ክፍል ውስጥ ገብቼ ተረጋግቼ ልማር የምችለው እንዴት ነው? ለሕይወቴ መፍራት ይመጣል:: እናም ሊሰማ የሚችለው በገዛ ሕይወቴ ላይ ስልጣን እንደሌለኝ ነው:: " ስትል ትናገራለች::

በዩኒቨርሲቲ ቆይታዋ እንደዚህ አይነት ነገሮች በመጀመሪያዎቹ ሶስትና አራት ዓመታት ተግዳሮት ሆነውባት እንደነበር በማስታወስ፤ እንደዚህ አይነት ነገር ዩኒቨርሲቲ ላይ የተለመደ ነው ትላለች:: አያይዛም በራስ አቅም ችግሩን ለመቅረፍ በመጣር ደህንነታቸው የተጠበቁ አካባቢዎች መምረጥ ይሻላል፤ እንጂ አንድ ጥቃት ከደረሰ በኋላ ምንም ማድረግ እንደማይቻል ትመክራለች::

"መጀመሪያ ላይ ትምህርቱን ስንጀምር የነበረን ሴቶች ቁጥራችን ጥቂት ነበር:: ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ዓመት እየሆንን ስንመጣ ቁጥራችን ጭራሽ እየመነመነ መጣ:: አራተኛ እና አምስተኛ ዓመት ስንደርስ ደግሞ ልጨርሺ ነው እንዴ፤ ለምን ንግድ ጀምረሽ አተይውም ይሉኝ ነበር:: ምናልባት ንግድ ህልሜ ቢሆን ጥሩ፤ ግን ሴት ስለሆንኩ አትችልም ብሎ ማሸፍ ፍታዊ ነው ብዬ አላምንም::" ስትል ትገልጻለች::

‹‹አሁን የመጨረሻ ፕሮጀክት እየሰራን ነው:: ለፕሮጀክቱ የመሰረት ነው ቡድን ውስጥ ብቻኛ ሴት እኔ ነኝ:: ብዙ ሴቶች በዘርፉ ከሌሉ እንዲአይነት ቡድኖች ውስጥ ብቸኛ ሴት የመሆን እድሉ ከፍተኛ ነው:: ›› ትላለች::

"ታዳጊ ሴቶች ሰው ህልማቸውን እንዲቀይር መፍቀድ የለባቸውም" የምትለው ተማሪ፤ አንድ ሰው ወዶም ይሁን ሳይወድ እሱ ይጠቅማል የሚለውን ነገር ለመናገር ይሞክራል:: ግን እንደዛ መሆን የለበትም ታዳጊ ሴቶች ማድረግ እንደሚችሉ እንዲያምኑ መፍቀድ ያስፈልጋል ትላለች::

"ጓደኛቸው ስላቆመች፣ ጓደኛቸው ስላልሆነች፣ እነሱ አይሆኑም ማለት አይደለም:: አርዓያ የሚሆን ሰው ባይኖራቸው እንኳን እራሳቸው ለታናናሾቻቸው አርዓያ መሆን እንደሚችሉ ማመን ትልቅ ነገር ነው::" ስትል ለታዳጊ ሴቶች መልክቷን ታስተላልፋለች::

የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ደግሞ በሚያጠኑበት ወቅት አልገባኝም ብለው ለሌላ ግዜ ማስቀመጥ ሳይሆን፤ በወቅቱ ተረድተው ለማለፍ ቢሞክሩ መልካም ነው:: ምክንያቱም ግዜ ካለፈ በኋላ ተመልሶ ለማንበብ ሊያስጠላ እና የበለጠ ሊከብድ ይችላል:: ነገር ግን በወቅቱ ተረድተው ካለፉ በፈተና ወቅት የሚጠበቀው መከለስ ብቻ ነው :: ሌላው ከዩቱብ ቪዲዮች ጋር እያቀያየሩ ማንበብ እና ከጓደኞቻቸው ጋር መጠያየቅ የተሻለ ውጤታማ እንደሚያደርግ ትገልጻለች::

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ግርማ መንግሥቴ**

ዛሬ ለማስታወስ የመረጥናቸው የአዲስ ዘመን ቀደምት ዘገባዎች በማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ሲሆን፣ ያነሳናቸው ነጥቦች ከበርካታ ጉዳዮች ጋር የሚያገናኟቸው ወፋፍራምም፣ ቀጫጭንም ክሮች ስላሏቸው በዛ መልኩ ይነበቡ:: ጋዜጣውም ያኔን ካሁን ጋር በማያያዝ ሚናው ይታወስ ዘንድ እያሳሰብን ወደ ይዘቶቹ እንሄዳለን። ከዛ በፊት ግን 1980ን ከሁሉም ልዩ የሚያደርገው አንድ መሠረታዊ ጉዳይ የነበረ ሲሆን፤ እሱም በቅርቡ በሞት የተለየው አሠልጣኝ አሥራት ኃይሌ መሪነት ኢትዮጵያ የምሥራቅና መካከለኛው አፍሪካ (ሴካፋ) ዋንጫን እራሷ አስተናጋጅ፤ እራሷም ዋንጫውን ወሳጅ በመሆኗ ምክንያት መላው ኢትዮጵያ ከደስታም በላይ በሆነ ደስታ የፈነጠዘችበት ልዩ ዓመት ነበርና ያንን የማይረሳ ታላቅ ድል ከጨዋታው በፊት ዋንጫው የእኛ ይሆን ዘንድ የተመኘውን ከሳምንት በኋላም ድሉን ተከትሎ የቀረበን ሌላ ግጥም እናስታውሳለን::

### ጠጅ ይመርመር

ሀገራችን የተለያዩ የባሕል ምግቦች እና መጠጦች ይገኙባታል። ከእነዚህም አንዱና ተወዳጁ የባሕል መጠጥ ጠጅ መሆኑ ይታወቃል። ጠጅ ሲዘጋጅ ከማር ሆኖ ጌሾ ብቻ እንደሚደባለቅበት ስለሚታወቅ ሌላ ቅመም ይታከልበታል የሚል ጥርጣሬ አልነበረም።

ይሁንና የጠጅ የጓዳ ምስጢር ከሆነና ለጠጅ ኃይል ለመስጠት (እንዲያሰክር) የተለያዩ ነገሮች እንደሚገቡበት ከተወራ ሰንበት ብሏል። በጠጅ ውስጥ ስለሚደባለቁት ኃይል ሰጭ ነገሮች እውቀት ባይኖረንም የጠጅ አጣጣል "ህቡዕ" ከወረደ ብዙ ጊዜ መሆኑን እናውቃለን።

ብዙ የኅብረተሰብ ክፍሎች በየእለቱ የሚጎነጩት ይህ መጠጥ [ጥንቃቄ] ከጎደለው ምን ያህል ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል መገመት አያዳግትም።

በጠጅ ውስጥ የሚጨመረውን ውሕድ በዓይን በማየት ለመለየት አስቸጋሪ ስለሆነ የጤና ተቆጣጣሪዎች ለናሙና ጠጅን እየወሰዱ በዘመናዊ መሣሪያ መመርመርና መቆጣጠር አስፈላጊ ይመስለኛል። ይህም ጠጪዎችን ግፋበት ለማለትና ለመገፋፋት ሳይሆን የኅብረተሰቡን ጤና ለመጠበቅ ከሚደረገው ጥረት አኳያ መታየት የሚገባው ነውና የጤና ተቆጣጣሪዎች የብርሌን ንፅሕና ብቻ ሳይሆን ውሃውንም ሊመረምሩት ይገባል እላለሁ።

**(መክት ጋሻዬ፣ አዋሳ፣ አዲስ ዘመን፣ ጥር 18 ቀን 1980 ዓ•ም)**

### በእሳት የመቃጠል አደጋ

የእሳት ቃጠሎ አደጋ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ይመጣል። አብዛኛውን ጊዜ የሚመጣው በፈላ ውሃ፣ ዘይትና ቅባት ባለው ፈሳሽ ምክንያት ነው። ለሎች መነሻዎች ደግሞ እሳት ወይም የነዳጅነት ባሕርይ ያላቸው ነገሮችና ፈንጂዎች ናቸው።

አደጋው በደረሰ ጊዜ እጅን በንፁሕ ውሃና ሳሙና ታጥቦ ንፁሕ ጨርቅ ወይም ፎጣ በጨው በተበጠበጠ ውሀ ውስጥ ነክሮ ቁስሉን ማጠብ ነው። ይህም ስቃዩን ያስታግስልዎታል። ቅባትና ቫዝሊን ማድረግም ቁስለኛውን ይረዳዋል። ነገር ግን ጥልቀት ያለው ቁስል ከሆነ ቅባቱን ወደ ውስጥ ለማስገባት ስለሚያዳግት በፔኒሲሊን ዱቄት ማከም የተሻለ ነው።

የተቃጠለው የሰውነት ክፍል በልብስ የተሸፈነ ከሆነ በቁስሉ አካባቢ የሚገኘውን ልብስ በስለት ቆርጦ ከሰውነት ላይ ማስወገድ ያስፈልጋል።

ልብሱ ከአካላቱ ጋር የተጣበቀ ከሆነ ግን ለማስለቀቅ ያለ መሞከሩ ይሻላል። ቁስሉን ከጀርሞች ለመጠበቅ ንፁሕ በሆነ ጨርቅ ጠምጥሞ ከተቻለ ወደ ሐኪም ቤት መውሰድ ነው። ቁስለኛው ወደ ሐኪም ቤት በሚሄድበት ጊዜም የቆሰለው ገላው ከጤናማው ሰውነቱ ጋር እንዳይነካካ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ቃጠሎውም በአጥንቱ መጋጠሚያ ላይ ከሆነ ቁስለኛው ቅልጥሙን ወይም ክንዱን እንዳያነቃንቅ ጠንከር ባለ ቅርፊት ወይም በእንጨት ስንጣቂ ደግፎ ማሰር ይረዳል።

ከዚህም ሌላ የመቃጠል አደጋ የደረሰበት ሰው በሰውነቱ ቆዳ ላይ በሚገኙ ወንፊት መሳይ ጥቃቅን ቀዳዳዎች አማካኝነት ብዙ ፈሳሽ ስለሚፈሰው ሰውነቱ እንዳይዝልና ብርድም እንዳይሰማው በቃጠሎ ምክንያት የተቀነሰበትን የፈሳሽ መጠን እንዲተካ መርዳት ነው። ይህንን ለማድረግም ብዙ ዘዴዎች አሉ።

አንዱ ዘዴ በተለይም ከባድ የመቃጠል ጉዳት የደረሰበት ሰው ከአንድ እስከ አራት ጠርሙስ ውሀ ማጠጣት ነው። ቢሆንም ውሀው ብቻውን ሳይሆን በእያንዳንዱ ጠርሙስ ከግማሽ እስከ አንድ ማንኪያ ጨው መጨመር ያስፈልጋል።

ሌላው ዘዴ ደግሞ ብዙ ስኳር ያለበት ትኩስ ሻይና ወተት በማጠጣት እቤት ውስጥ ወይም ከጥላ ስር አመቻችቶ ማስተኛት ሊሆን ይችላል። ይህ ሁሉ የሕመምተኛውን ስቃይ ይቀንስለታል። ያም ሆነ ይህ አደጋው የአካል ጉድለት፣ ሞትና የኑሮ ችግር ሊያመጣ ስለሚችል በእሳት በምንገለገልበት ጊዜ በጣም መጠንቀቅ ይኖርብናል።

**(አዲስ ዘመን፣ ታኅሣሥ 15 ቀን 1980 ዓ•ም)**

የኛው ትሁን!
የሀገር ፍቅር ❖❖❖ የጽናቱ
የወገን ፍቅር ❖❖❖ የጥልቀቱ
ትላንት ዛሬ ❖❖❖ ነገም ❖❖❖ ተነገ ወዲያ
ከሀገር ድንበር ከዚያ ❖❖❖ እዚያ
ሰንደቅ ቆሞ ❖❖❖ በሰንደቅ ላይ
የሀገር ሲሳይ ❖❖❖ የዘር ክፋይ።
ስታደሚ ❖❖❖ በፍቅር ፊት
አሁንም ❖❖❖ አሁንም ❖❖❖ አሁንም ወደ ፊት
ሙሽራዬ ❖❖❖ የኔ ሎጋ
አበባዬ ❖❖❖ የኔ ሽጋ
ነገም ❖❖❖ ወዲያው ❖❖❖ ወደኛ ጋ!
ሆ! እንበል ❖❖❖ በምድራችን
በእግር ኳሱ ሜዳ ❖❖❖ በቀዬአችን
❖❖❖❖❖❖❖❖❖ ሙሽራዬ
❖❖❖❖❖❖❖❖❖ አበባዬ
የእኛ ትሁን የእማማዬ
ዛሬም በሜዳችን ❖❖❖❖❖❖❖❖❖
ገድል ይዘን ❖❖❖ ገድል ቋጭተን
እማማችን፤ ❖❖❖ ከአፍሪካ ❖❖❖ ይዋል ስሟ
በምድራችን እናም ❖❖❖
አደራ ነው ❖❖❖ ለሕዝብ ፍቅር
አደራ ነው ❖❖❖ ለሀገር ክብር
ተጫዋቹ ወገናችን ❖❖❖
የእኛው ክፋይ ልጃችን
ለድል ጥቢ ❖❖❖ ለድል ብሥራት
ለሀገር ክብር ❖❖❖ ለወገን ኩራት
ዛሬም ❖❖❖ እንደ ትናንት ❖❖❖ በምድሯ
በአየሩ ዓውድ ❖❖❖ በእምባችን
ሐሴትን አፍርተህ ሐሴትን ለግሰን
❖❖❖❖❖❖❖❖❖ ሙሽራዬ
❖❖❖❖❖❖❖❖❖ አበባዬ
የእኛ ትሁን የእማማዬ።
አዎ ❖❖❖
የኛ ትሁን ❖❖❖ ዋንጫይቱ
አደራ ይዛችሁ ባደራ ላይ
❖❖❖❖ ወገኖቼ ተበራቱ
ከኃይለየሱስ ጌታሁን (4 ኪሎ)
(አዲስ ዘመን፣ ታኅሣሥ 18 ቀን 1980 ዓ.ም)

# ዓለም አቀፍ



## ፖሊስ 'ሕገወጥ የማዕድን ቆፋሪዎችን' ከማዕድን ማውጫ ለማስወጣት ምግብ እንዲቋረጥባቸው አደረገ

የደቡብ አፍሪካ ፖሊስ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሕገወጥ የማዕድ ቆፋሪዎችን ምግብና ውሃ በማቋረጥ ከነበሩበት የማዕድን ማውጫ እንዲወጡ በማስገደድ በቁጥጥር ስር ማዋሉን ገለጸ።

የደቡብ አፍሪካ ፖሊስ ሕገወጥ የማዕድን አውጪዎችን በቁጥጥር ስር ለማዋል በወሰደው ምግብና ውሃ የማቋረጥ ርምጃ 540 ግለሰቦች በቁጥጥር ስር የዋሉ ሲሆኑ ከሥራ ውጭ ከተደረገ የማዕድን ማውጫ እንደነበሩም ተገልጿል።

የፀጥታ ኃይሎች በዚህ ሳምንት መጀመሪያ ላይ ማዕድን አውጪዎቹን ከጉድጓዱ ውስጥ ለማስወጣት ሲሉ ምግብ እና ውሃ እንዳይቀርብላቸው ከልክለዋል።

"ረሃብ እና የውሃ ጥም" ያጠቃቸው የማዕድን ቆፋሪዎች ከጉድጓዱ ለመውጣት መገደዳቸውን ፖሊስ ተናግሯል።

ከቅዳሜ ጀምሮ በሰሜን ኦርክኒ ከተማ ውስጥ ከሚገኘው የማዕድን ማውጫው ውስጥ አንድ በአንድ መውጣት ጀምረዋል። አሁንም ግን በመቶዎች የሚቆጠሩ በማዕድን ማውጫው ውስጥ እንዳሉ ይገመታል።

እሑድ ዕለት የሀገሪቱ የፖሊስ አዛዥ የፀጥታ ኃይሎች ከኃላፊነታቸው "ወደ ኋላ እንዳይሉ" እና "የሕግ የበላይነት መከበሩን እንዲያረጋግጡ" ባወጡት መግለጫ ጠይቀዋል።

መግለጫው አክሎም በዚህ ሳምንት መጀመሪያ ላይ የፀጥታ ኃይሎች "ከሥራ ውጭ በተደረጉት የማዕድን ማውጫዎች አካባቢ ያሉ ማኅበረሰቦች ምግብ፣ ውሃ እና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን ለሕገ-ወጥ ማዕድን አውጪዎች እንዳያደርሱ አግደዋል" ብሏል።

ቅዳሜ ዕለት 225 ማዕድን አውጪዎች መውጣታቸወን ፖሊስ ገልጿል። አሁንም ግን "ሺህ እንኳን ባይሆኑ በመቶዎች የሚቆጠሩ" ከመሬት በታች ናቸው ተብሎ ይታሰባል ሲል አክሎ ነበር።

ፖሊስ እሑድ ዕለት በሰጠው መረጃ ከማዕድን ማውጫው ውስጥ ተጨማሪ 340 ሰዎች መውጣታቸውን እና በቁጥጥር ስር መዋላቸውን ገልጿል።

"ዛማ ዛማስ" (በዙሉ ቋንቋ ዕድላቸውን የሚሞክሩ እንደማለት ነው) በመባል የሚታወቁት በሺዎች የሚቆጠሩ ሕገ-ወጥ ማዕድን ማውጫዎች በአካባቢው ይንቀሳቀሳሉ።

የፖሊስ ኮሚሽነሩ ሌተናል ጀነራል ሻድራክ ሲቢያ እንደገለጹት ከሆነ ከታኅሣሥ 2023 ወዲህ በሰባት ግዛቶች ከ13 ሺህ 690 በላይ ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ስር ውለዋል።

"283 ዶላር በጥሬ ገንዘብ እና ያልተቆረጡ እና 1.8 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጡ አልማዞች ይዘናል" ብለዋል።



## የስፔን ተቃዋሚዎች በንጉሡና ንግሥቲቷ ላይ ጭቃ ወረወሩ

ከሁለት መቶ በላይ ሰዎች ለሞቱበት የስፔኑ የጎርፍ አደጋ የተሰጠው ምላሽ በቂ አይደለም ያሉ ተቃዋሚዎች በንጉሡና ንግሥቲቱ ላይ ጭቃ ወረወሩ።

ንጉሡና ንግሥቲቱ በከፋ የጎርፍ አደጋ የተመታችውን የቫሌንሺያ ግዛት ለመጎብኘት በሄዱበት ወቅት ነው የተቆጡ ተቃዋሚዎች ጭቃ እና ሌሎች ነገሮችን የወረወሩባቸው።

ንጉሣውያኑ ጥንዶች፣ የስፔን ጠቅላይ ሚኒስትርና ሌሎች መሪዎች ፓይፖርታ የተሰኘችውን ከተማ እየጎበኙ ባለበት ወቅት "ነፍሰ ገዳይ" እና "እፈሩ" የሚሉ ስድቦችን ከተቃዋሚዎች ተሰንዝሮባቸዋል።

ንጉሥ ፌሊፔና ንግሥት ሌቲዚያ ፊታቸውና ልብሳቸው ጭቃ ተለውሶ ጉዳት የደረሰበትን ማኅበረሰብ ሲያጽናኑ ታይተዋል።

ባለፉት አስርት ዓመታት ውስጥ የከፋ ነው በተባለው በዚህ ጎርፍ ከ200 በላይ ሰዎች ሕይወታቸው አልፏል። የነፍስ አድን ሠራተኞች በሕይወት ያሉ ሰዎችን ለመታደግ እንዲሁም አስከሬኖችን ለማውጣት በመሬት ስር ባሉ የመኪና ማቆሚያ ስፍራዎች እና መተላለፊያ ዋሻዎች ፍለጋቸውን ቀጥለዋል።

ጎርፉን አስመልክቶ ማስጠንቀቂያ አልነበረም በሚል እንዲሁም ለአደጋው የተሰጠው ምላሽ በቂ ባለመሆኑ ከፍተኛ ቁጣ ተፈጥሯል።

ንጉሡ ከመኪናቸው ወርደው በጠባቂዎቻቸውና በፖሊስ ታጅበው በእግረኛ መንገድ ላይ ሲጓዙ የተቆጡ በርካታ ተቃዋሚዎች ጭቃ እየወረወሩ፣ ዘልፈዋቸዋል፡፡

ጠባቂዎቻቸው እና ፖሊሶች ንጉሡን ከበው ቀለበት በመሥራት ከተቃዋሚዎቹ የሚወረወርባቸውን ጭቃ እና ቁሳቁሶች ለመከላከል ሙከራ አድርገዋል፡፡

ንጉሡ የሚወረወርባቸውን ጭቃ፤ ዘለፋና ስድብ ተቋቁመው በርካቶቹን አዋርተዋል፤ አለፍ ሲልም እያቀፉ አፅናንተዋል፡፡

የስፔኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ፔድሮ ሳንቼዝ እና የቫለንሺያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ካርሎስ ማዘን በጉብኝቱ ላይ ንጉሣውያኑ ጥንዶችን ተቀላቅለው የነበረ ቢሆንም የተቃዋሚዎች ቁጣ መጠንከሩን ተከትሎ ከስፍራው በፍጥነት እንዲወጡ ተደርገዋል።

# ስፖርት






## የመም ውድድሮችን ያነቃቃል የተባለው ‹‹የግራንድ ስላም›› ፉክክር

ቦጋለ አበበ

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በረጅም ርቀት የመም (ትራክ) ውድድሮች በዓለም ላይ እየቀነሱ መሄዳቸው የርቀቱ ከዋክብት አትሌቶች ላይ የፈጠረው ተፅዕኖ በግልፅ ታይቷል። በዚህ ምክንያት በርካታ የትራክ አትሌቶች በጊዜ ፊታቸውን ወደ ጎዳና ላይ ውድድሮች ለማዞር ተገደዋል። ይህም እንደ ኢትዮጵያና ኬንያ ያሉ ሀገራት ዓለም አቀፍ የመም ውድድሮች ላይ ያላቸውን ውጤት በማቀዛቀዝ ረገድ ትልቅ ተፅዕኖ እንዳሳደረ የብዙዎች እምነት ነው። ይህም ኦሊምፒክንና የዓለም ሻምፒዮናን በመሳሰሉ ውድድሮች ታይቷል፡፡ ከዚህም ባለፈ የረጅም ርቀት በተለይም የ5 እና 10 ሺ ሜትር ውድድሮች ከኦሊምፒክ የመሰረዝ አደጋ እንደ ተጋረጠባቸው ሲነገር መቆየቱ ይታወቃል፡፡

ሰሞኑን ከወደ አሜሪካ የተሰማው ዜና ግን የመም ውድድሮችን ያነቃቃል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበታል፡፡ በመም ውድድሮች ታሪክ ከፍተኛ ሽልማት የሚያስገኘው ‹‹የግራንድ ስላም›› ውድድር በመጪው ሚያዚያ ወር በአሜሪካ እንደሚጀመር ይፋ ተደርጓል፡፡

ይህ ውድድር በቅርብ ዓመታት በውድድር ቁጥር ማነስ ምክንያት እየተቀዛቀዘ የነበረውን የትራክ ሩጫ ያነቃቃል ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን፣ በቀድሞው የአራት ጊዜ የኦሊምፒክ አሸናፊ አትሌት ማይክል ጆንሰን የተመሠረተ ነው፡፡ የትራክ ግራንድ ስላም ውድድር እ.ኤ.አ በመጪው ሚያዚያ 2025 የትራክ እና የሜዳ ተግባራት ፉክክሮችን አካቶ እንደሚካሄድም ታውቋል፡፡




**ፅጌ ገብረሠላማ በውድድሩ ስመካፈል የተመዘገበች የመጀመሪያዋ አትሌት ሆናለች፣**

ውድድሩ የተነደፈው የመም ተፎካካሪ አትሌቶች የመታየት እና የስፖንሰርሺፕ ዕድሎችን እንዲያገኙ ለመርዳት ሲሆን፣ በአራት ዓመት አንድ ጊዜ ከሚካሄደው ኦሊምፒክ በተቃራኒው የግራንድ ስላም ትራክ ሊግ በዓመት አራት ጊዜ ይካሄዳል። ይህም ትልልቅ አትሌቶች በተደጋጋሚ እርስ በእርስ እንዲፎካከሩና የተለያዩ ዕድሎችን እንዲያገኙ ዕድል ይከፍታል ተብሎ ታምኖበታል።

ውድድሩ በሁለቱም ፆታዎች ከ100 ሜትር እስከ 5 ሺህ ሜትር ድረስ የሚሮጡ አትሌቶች በውድድር ዓመቱ ባስመዘገቡት የተሻለ ሰዓት መሠረት ተጋብዘው ወይም በማኔጀሮቻቸው አማካኝነት የመካፈል ዕድል እንዲያገኙ ይረዳል።

ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ፅጌ ገብረሠላማ በዚህ ውድድር ላይ አስቀድማ በመመዝገብ የመጀመሪያዋ አትሌት መሆኗ ታውቋል፡፡ ልክ እንደሷ ሁሉ ከመም ውድድሮች ወጥተው በጎዳና ላይ ውድድሮች ትኩረታቸውን ያደረጉና ለማድረግ ያሰቡ በርካታ ከዋክብት አትሌቶችም ወደ ትራክ ውድድሮች እንደሚመለሱ ይጠበቃል፡፡

በተደጋጋሚ የትራክ ውድድሮች ቁጥራቸው እየቀነሰ ነው ለሚሉ አሠልጣኞች እና አትሌቶች ይህ ውድድር የተሻለ ዕድል ይዞ እንደመጣም የተለያዩ የአትሌቲክስ ባለሙያዎች አስተያየት ሰጥተውበታል፡፡

በአጠቃላይ 96 አትሌቶች የሚካፈሉበት አዲስ የትራክ ግራንድ ስላም ሊግ በአራት ግራንድ ስላም ውድድሮች የመጀመሪያ ዓመት እስከ 12.6 ሚሊዮን ዶላር ሽልማት ማዘጋጀቱ ተዘግቧል፡፡ በእያንዳንዱ ውድድር በድምሩ 3 ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ ለሽልማት ቀርቧል።

በሎስአንጀለስ ከተማ መቀመጫውን ያደረገው የትራክ ግራንድ ስላም ውድድር ከ30 ሚሊዮን ዶላር በላይ ኢንቬስትመንት ለውድድሩ እንደሚያዘጋጅም አረጋግጧል።

ሌትስ ረን የተባለው የአትሌቲክስ ድረ ገፅ ባሳለፍነው መስከረም ወር ባወጣው መረጃ መሠረት ውድድሩ በሎስንጀለስ፤ ኒውዮርክ፣ ጃማይካ ኪንግስተን እና በእንግሊዝ በርሚንግሃም በሚያዚያ ወር ሁለት ሳምንት እና በግንቦት ወር ሁለት ሣምንት እንደሚካሄድ ዘግቧል።

የትራክ ግራንድ ስላም ውድድር አትሌቶች በአንድ የውድድር ዘርፍ አራቱን የግራንድ ስላም ሊጎች ቢያሸንፉ 400 ሺህ የአሜሪካ ዶላር ያገኛሉም ተብሏል። በአንድ ሊግ የግራንድ ስላም የሽልማት ገንዘብ 1ኛ 100 ሺህ የአሜሪካ ዶላር፣ 2ኛ 50 ሺህ የአሜሪካ ዶላር፣ 3ኛ 30 ሺህ የአሜሪካ ዶላር፣ 4ኛ 25 ሺህ የአሜሪካ ዶላር፣ 5ኛ 20 ሺህ የአሜሪካ ዶላር፣ 6ኛ 15 ሺህ የአሜሪካ ዶላር፣ 7ኛ 12 ሺህ 500 የአሜሪካ ዶላር፣ 8ኛ 10 ሺህ የአሜሪካ ዶላር እንደሚሆን መረጃዎች አመልክተዋል፡፡